

# ቂመኛው ፓትርያርካና በቀሉ!



ርዕሰ አድባራት ደብረጽዮን ቀስት ማርያም ያደረገችው መከላከል

ወንድሙ መኰንን፣ ለንደን የካቲት 2003 ዓ.ም.

## መቅደም

“ውሀ ከጥሩ ነገር ከሥሩ” ይባላል። ይኽ ጽሑፍ ቤተክርስቲያናችን፣ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረጽዮን ከጥቅምት 14 ቀን 1985 ዓ. ም. (24 October 1993) ጀምራ እስከዛሬ የተቋቋመችውን ፈተና በአጭር በአጭሩ ያትታል። የዛሬ ችግራችን አሁን በድንገት የተከሰተ ሳይሆን የታጋይ ጳውሎስ ያደረ ቂም የዞረ ድምር ነው። ስለዚህም ጽሑፉ ሊርዝም ይችላል። ቆራርጦ በክፊል በክፊል ማውጣቱ ታሪኩን ስለሚያንዛዛው፣ አንባቢው ሁሉን መረጃ በአንድ ቦታ ማግኘት እንዳለበት ታምኖ ነው በአንድ ላይ እንዲወጣ የወሰነው። ለማንበብም እንዲያመች በመጠነኛ ንዑስ ርዕሶች (manageale size) ተከፋፍሏል። እንግዲህ፣ አንባቢ እያረፈ፣ እንደ አንድ አነስተኛ መጽሐፍ ውሰዶ፤ መረጃዎቹን እየመረመረ ማንብብ ይችላል። ወደፊትም በመጣጥፍ (booklet) መልክ ታትሞ ሰው እጅ ለማስገባት ዕቅድ አለ። መልካም ንባብ።

## መግቢያ

ተፈጥሮን ተመክሮ መች መልሶት! የድሮው አባ ገብረመድኅን፣ የዛሬው ታጋይ ጳውሎስም፣ ገና ከጀምሩ፣ ገና ከጠዋቱ የሀይማኖት አባትነት ይቅርና፣ የአንድ የተራ የክርስቶስ ተከታይ ምግባርና ትሕትናን አልተያባቸውም። ሳይበቁ መነኰሱ፣ ሳይገባቸው ጰጰሱ፣ በጉልበታቸው ፐተረኩ። ስለሳቸው ያለን መረጃ በሙሉ የዚህ ዓለም ሰው እንደነበሩና ዛሬም እንደሆኑ ያስረዳል። ለዚህ ዓለም ድሎት ተመቻችቶ የተፈጠረው ተክለ ሰውነታቸው፣ እንደመነኰሴ ደረቅ ዳቦ ሳይሆን፣ ዘመናዊ ኬክ የሚቀርብለት፣ የሚጠጡት ንጹሕ ውሀ፣ ወይም ግፋ ቢል የአገራችን የቤት ጠላ ሳይሆን፣ በስኮትላንድ የተጠመቀ ሲንግል ሞልት ውስኪ፣ የሚጓዙበት ቤተክርስቲያኗ ባዘጋጀችላቸው መኪና ሳይሆን፣ የሆሊውድ ተዋናዮች፣ ከአንደ በላይ ውድና በልዩ ትዕዛዝ ተሠርተው በተገዙ ጥይት በማይበሳቸው መኪኖች ሁኖ፣ በቁማቸው እንደ ናቡከደነጾር ሀውልት ያሠሩ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ናቸው። የቅንጦት አኗኗራቸው ሲታይ ለራሻው ራስፑቲን ምስጋና ይንሳው ያሰኛል። አባ ጉልቤው ጳጳስ ስልጣንም የያዙት ተጸልዮላቸው፣ ብጽዓን አባቶች ሱባዔ ገብተውላቸው፣ መንፈስ ቅዱስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶላቸው ሳይሆን፣ ታጋይነታቸው በወያኔ ዘረኛ ወንበዴዎች ተረጋግጦላቸው “መፈንቅለ መንበር” ፈጽመው፣ በወያኔ ወታደር ታጅበው፣ በጉልበታቸው ነበር።

ብርሃኑ ሠርፁ “የደርግ የእስራት ዘመን” በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፣

> *“የደረደሩትን ሳሙናና ማስዋቢያ ተጠቅመው ኢስኪጨርሱ መጠበቁ እልህ የሚያስጨርስ ነበር። አንድ ቀን አንድ እስረኛ (ወታደር) ምርጫ አጥቶ ከሳቸው በኋል ተራ ለመታጠብ ሲጠብቅ፣ ሲኳኳሉና፣ አንዴ ሽቶ አንዴ ዲኦደራንት ሲቀባቡ፣ በጭራሽ የማይለቁ ሆነውበት ትዕግስቱ ያልቅና፣ ‘ምነው አባታችን? ቶሎ ብለው ይጨርሱና እኔም ልታጠብ እንጂ! እኔ እርስዎን ስጠብቅኮ ቆሜኮ ከኔ በኋላ የመጡት ሁሉ እየጨረሱ ሄዱኮ፤’ ብሎ ቆጣ ብሎ ይናገራቸዋል። እሳቸውም እንደ ሃይማኖት አባት ሳይሆን እንደ ማንኛውም ጎረምሳ፣ ‘ሳልጨርስ ልለቅልህ ነው? ረጋ ብዬ እለቅልሃለሁ፤ ከቸኮልክ ሌላ ጋ ሂደህ ወረፋ ጠብቅ፤’ ብለው አመነጫጭቀው ይመልሱታል። ነገሩ በዚህ ቀጥሎ፣ ይካረሩና ከጥቂት መሰዳደብ በኋላ ለጠብ መገባበዝ ላይ ሲደርሱ፣ አባ ሆዬ ‘ቀሚስ ብለብስ ሴት መሰልኩት እንዴ?’ ብለው ፎክረው የቀሚሳቸውን እጅጌ ጠቅለል ጠቅለል አድረገው፣ ቦክስ ሊገጥሙ ሲሉ፣ እዚያው የነበሩ ሰዎች በመካከላቸው ገብተው፣ “እንዴ! ነውር አይደለም እንዴ በዚህ ሁኔታ እያለን መደባደብ፣ ደሞ እርሶስ ቢሆኑ መደባደብን ምን አመጣው?” ብለው ሁለቱንም ተቆጥተውና መክረው ለመገላገል ሲሞክሩ፣ ከወጣቱ ወታደር ይልቅ ለገላጋይ ያስቸገሩትና ካልተደባደብኩ ብለው ሲጋበዙ የነበሩት አባ ጳውሎስ ነበሩ። (ገጽ 123)*

በዚህ የብርሀኑ ሠርጹን የእስር ቤት ትዝታ መጽሐፍ ውስጥ ይኸንን እንዳነበብኩ፣ እንደ አንድ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ዕምነት ተከታይ ከማፈርና ከመሸማቀቅ ባሻገር የተሰማኝ ነገር ቢኖር፣ አባ ገብረመድህን (ታጋይ ጳውሎስ) በፍጹም ሳይበቁ የመነኰሱ ዓለማዊ ሰው መሆን አለባቸው የሚል ስሜት ነበር። እኚህ ሰው በጉልበታቸው የቤተክርስቲያኗ ርዕስ ከሆኑ ጀምሮ፣ ብዙው አማኝ በዕምነቱ ግራ ተጋብቶ፣ ግማሹ፣ ሲኮተልክ፣ ግማሹ ጸንጥጧል። አንዳንድ ወጣቶች እስከነአካቴው ሰለመዋል። ጌታ ዳግም ተመልሶ ሲመጣ፤ "የታሉ ጠቦቶቼ! የታሉ ግልገሎቼ! የታሉ በጎቼ" ሲላቸው፣ እኚህ ዓለማዊ ሰው ምን ይሆን መልሳቸው?

## የቂሙ ቋጠሮ ውል



ታጋይ ጳውሎስ፣ በወያኔ ዘረኞች ቡደን እየታገዙ ሕጋዊውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶስ ተዋኅዶ ፓትርያርክ አቡነ መርቆሪዮስን ገልብጠው በትረ ፕትርክናውን ከጨበጡ ቀን ጀምረው፣ ቤተክርስቲያኗን እያመሱ፣ ቀኖናዋን እያፈረሱ፣ ቅዱሳንን ከማዋከብ አልፈው እስከመግደል (የባህታዊ ፈቃደስላሴን ነብስ ይማርልን) የደረሱ ሲሆኑ 20 የጭንቅ ዓመታትን አስቆጥረው በቁማቸው ሐውልት ለማሠራት በቅተዋል። ታዲያ የወያኔ መንጋ በዓለም ዙሪያ እየዞረ፣ የኢትዮጵያን ንበረት የሆነውን ሁሉ (ቤተ እስራኤላውያን የተሸጡበት ገንዘብ ሳይቀር) ይገባኛል ብሎ ሲመዘበር፣ የድሮው አባ ገብረመድኅንም (የአሁኑ ታጋይ ፖውሎስ) በበኰላቸው ዓለምን እየዞሩአት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አጸደ ዕምነቶችን ከነጥሬ ሀብታቸው ይገባኛል በማለት ማገበስበሱን ተያያዙት። ዳሩ ግን፣ ዕድላቸው ከፍቶ ለንደን ላይ ሲደርሱ ዕቅዳቸው ከመክሸፍም አልፎ ክፉኛ ባረቀባቸው። ሙከራቸው ቀላል አልነበረም። የዛሬው በአየርላንድ የወያኔ ዲፕሎማት፣ ሙሉጌታ አሥራተ፣ ለንደን ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያምን ለታጋዩ አባ ጉልቤ ከነንብረቷ ሊያስረክብ ከሳቸው ግር እላይ-እታች ተሯሯጠ። ሕዝብ "አይሆንም" አለ። "አይምጡብን" አለ። ግርግር ተነሳ። ሕዝቡ ተንኰላቸው ስለገባው አስመሳዩን ጳጳስ እዚያች ቦታ ድርሽ እንዳይሉ ቢያስጠነቀቁም እነሙሉጌታ አስራተ በጎን ፖሊስ ጠርተው ጥቅምት 14 ቀን 1985 ዓ. ም. (24 October 1993) ይዘውአቸው በድፍረት ከቸች አሉ። ይኽቺን ይወዳል ለንደን! ታጋዩ ጳጳስም ሕዝቡን ንቀው ገብተው ሊቀድሱ ሲሞክሩ፤ የዱላ ውርጂብኝ ወረደባቸው። ጫማ ሳይቀር ተወረወረባቸው። ቆባቸው ከጭንቅላታቸው ላይ በረረች። ክብራቸው ተገፈፈ። ቆሌአቸው እርቃኑን ቀረ። አንድ ወንድም እንደታዘበው የሚወረወር ሲጠፋ መጽሐፍ ቅዱስ አንስተው የወረወሩባቸውም አልጠፉም። በፖሊስ ኃይል፤ በሠላጠኑ ዎሾችና በእነ በሙሉጌታ አሥራተ ተጠበቁ። በእልህም ጳጳስ ተብዬው ታጋይ ወያኔ፣ ሕዝቡ እየጨኸባቸው በትዕቢት ውሾች እና ፖሊሶች ዘብ ቁመውለቻው ቀደሰኩ ብለው ቅዱሱን ቁርባን በከለባት አረከሱት። ፖሊሶችና ውሾች ሕዝቡን ከበው አፈጠጡበት። "አገቱኒ ከለባት" ይሉሀል ይኸው አይደል? ጨርሰው ሲወጡም አንድ አባት ፓትርይርኩን የተጠናወታቸውን ሰይጣን ሊያስለቅቁአቸው ነው መሰል፣ ለእሳት ማጥፊያ በተዘጋጀ ልዩ ወሀ (ሲቀደስበት ዓመታት አልፈውት ወደፀብልነት ሳይቀየር ይቀራል?) ሊረጩአቸው ሲዘጋጁ ፖሊስ ተረባርቦ አስጣላቸው።

በዚያ ግርግር የተነሳ ቤተክርስቲያኗ ስድስት ሰዎች ታሠሩባት። ጀግኖቹ የሎንደን ልጆችን፣ ታጋይ ፖውሎስ ተረማመደዋቸው እንደተዘባነኑ እንደማይሄዱ አረጋገጡላቸው። ወያኔም ለንደን የማትቆረጠም ባቄላ መሆኗን ትምሕርት ተማረች። በፖሊሶችና በውሾች ሕይወታቸውን የታደገችላቸው ታጋዩ ፓትርያርክ ግን ቂማቸውን እንደቋጠሯት ከዚያች ቅድስት ስፍራ፣ ዲያብሎስ ሲረታ ተሸማቅቆ እንደሚጠፋ ሁሉ፣ ሹልክ ብለው እብስ ጥርግ አሏት።



THE DAILY TELEGRAPH

MONDAY OCTOBER 25, 1993

## Six held in Ethiopian Church row

By Tim King

A REPRESENTATIVE of the Archbishop of Canterbury was caught up in ugly scenes surrounding yesterday's morning service at the Ethiopian Orthodox Church in London where police arrested six people.

Dr Richard Marsh, the Archbishop's assistant secretary of ecumenical affairs, had gone to the church in Down Street to greet Patriarch Paulos, who arrived in Britain last Tuesday. The church is leased by the Diocese of London to the Ethiopians.

Dr Marsh was met by supporters of a faction of the Ethiopian Orthodox Church which refuses to recognise the authority of Patriarch Paulos.

When the Patriarch arrived to take the service the demonstrators tried to prevent him entering the building. He managed to enter the church only with the help of police, who could not prevent demonstrators bursting in after him.

As police tried to mediate between the factions, they asked Dr Marsh, who is a priest of the Church of England, to convey messages to the Patriarch as he stood in the inner sanctum.

The Patriarch refused to leave the church until he had finished saying the liturgy.

Dr Marsh said: "There was an awful lot of shouting and confrontation. It was very aggressive." He said on behalf of the archbishop: "We are very distressed to see such incidents taking place in God's house."

Riot police were deployed in Savile Row to separate the warring factions.

There were five arrests and two men were charged. The others were later released.

When the Patriarch left the church after reciting the three-hour liturgy, a man smashed the side window of his car. He was arrested and then released on bail.

The Patriarch returned to Addis Ababa last night.

ይኸ ትርዒት ከተፈጸመ በኋላ የታጋይ ፓውሎስን ሰዎች አልተገላገልናቸውም። እነዚያ የታጋዩ ፓትርያርክ ጉዳይ አስፈጻሚዎች እዚያች ተጎሎተው በየቅዳሴው ሥነ-ሥርዓት ስማቸው እየተጠራ እየተጸለየላቸው እንዲቀጥል ዘብ ተገተሩላቸው። "ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት ላሳር ነው" ብለው ብዙ መኳንንትና ወይዛዝርት ምዕምናን የታጋይ ጳውሎስ ስም እየተጠራባቸው ላለመጸለይ ቤተክርስቲያኗን ጥለው ሄዱ። አንዳንዶቻችን ግን፣ "ወያኔ ከአገራችን አሰደደን። ደግሞ እዚህ አገር መጥተን በስደት ስንኖር፣ ገንዘባችንን እያዋጣን ያቋቋምናትን ቤተክርስቲያን ጥለን የት እንሂድላቸው?" በማለት ስማቸው ሲነሳ ቃር ቃር እያለን ቁመን፣ ለሌሎች ቅዱሳን መጸለይ ሲጀመር እራሳችንን ዝቅ ዝቅ ማድረግ ገባን። በዚህ ሁኔታ ለ12 ዓመታት ቀጠልን። የለንደኗ ደብረ ጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስትያን ተአምረኛ ናት! ተአምሯን ለማየት በትዕግስት ጠበቅን። አላሳፈረችንም።

ከዘረኝነት በአሻገር፣ እኛ ተራዎቹ ኢትዮጵያውያን ከወያኔ የምንለይባት አንዲት ተጨማሪ ቁምነገር አለች። ወያኔ መሸነፍን ተቀብሎ ጨርሶ ተስፋ አያቆርጥም። ክርስቲያናዊ ተስፋ አይደለም ታዲያ! ዲያብሎሳዊ ተስፋ አለመቁረጥ እንጂ! ውርደት ምሳው፣ ውርደት እራቱ በመሆኑ፣ ውርደት አያሳፈረውም። አባላቱ ለሥልጣንስ የበቁት በዚሁ ዜዴ አልነበር? አለቀላቸው ሲባል፣ ልክ እንደ አባቢቱ አቧራዋን ቅመው ነፍስ ይዘራሉ። በተሸነፉ ማግስት ቁጭ ብለው እንዴት እንደገና እንደሚሞክሩ ሸሪቱን ሲሸርቧት ያድራሉ። የወያኔ ሰዎች በሙሉ ዓይናቸውን በጨው ያጠቡ ዓይን አውጣ ጩሉሌዎች ናቸው። አንድ ጊዜ አንድ ነገር ለመንጠቅ ተነስተው ሲሞክሩ ሕዝቡ ተረባርቦ ሲያስጥላቸው፣ እንደገና ተስፋ ሳይቆርጡ መልሰው መላልሰው እጃቸው ለማስገባት ከመሞከር ጨርሶ አያርፉም። የሠራተኛውን ማኅበር በዚህ ሁኔታ ነበር ያንበረከኩት፣ የመምህራን ማኅበርን ለ15 ዓመታት ታግለውት በመጨረሻ ባዶ እጁን ያስቀሩት በዚህ ዘዴ ነው። ታጋዩ የወያኔ ፓትሪርክም ከዚያው ምንጭ የተቀዱ መሠርይ የለየላቸው ወያኔያዊ ሰይጣን የተጠናወታቸው ስለሁኑ እንዲሁ ከዚያች ተዋርደው ከወጡ በኋላ ተስፋ ቆርጠው አፍረው አልቀሩም። በየጊዜው ቤተክርሲያኗን በእጃቸው ለማስገባት ከመሞከር፣ ሰው እየሾሙ ከመላክ፣ ከውስጥ ቦርቧሪ ሆዳም መልምለው ከማስነሳት አንዳችም ቀን ቦዝነው አያውቁም። ቤተክርስቲያኗን እጃቸው አያስገቡ እንጂ፣ መመልመል አላስቸገራቸውም። ማርያም ተአምረኛ ናት። ልጇ በስሟ የተጠራላትን ቤተክርስቲያን ከዲያብሎስ እየጠበቀ፣ ልጆቿን እስካሁን ተንከባክቧቿቸዋል። ወደፊትም ይንከባከባቸዋል።

# ካህኑ ካድሬ፣ ብሬ

ታጋይ ፓውሎስ አድፍጠው ለንደን ደብረጽዮን ቅድስት ማርያምን ሊበቀሉ እንዳሸመቁ፣ ታኅሣሥ 15 ቀን 1990 (24 December 1997) ዓ.ም የደብሩ አስተዳዳሪ አቡነ ዮሐንስ (አባ አረጋዊ) በቤታቸው እንዳሉ በአጠራጣሪ ሁኔታ ሙተው ተገኙ። ምዕምናን ተደናገጡ። የሚይዙትን የሚጨብጡትን አጡ። በጊዜው የነበሩ ካህናት፣ ሕዝቡን በማረጋጋት፣ አጽናኑት። እነዚህ ካህናት ያደረጉት መረባረብ፣ ምንጊዜም የሚረሳ አይደለም። አቡነ ዮሐንስ ትተው ያለፉትን ክፍተት ሸፍነው ተተኪ አቡን ከኢትዮጵያ ሲኖዶሱ እስኪላክ ተብሎ ተንከባክበው ያዙን። እኛም ተጽናናን። “እረ  የምን አቡን?” አልን።

ጊዜው ሄደ። ገሰገሠ። ሁዳዴ ጾም ገባ። ምዕምኑም እነዚያን ስምንት ሳምንታት ቤተክርስቲያን በመመላለስ በጸሎት፣ በምህላና በሱባዔ ጊዜውን ማሳለፍ ተያያዘው።  ስድስተኛው ሳምንት ላይ አንድ ጉድ ፈላ። ምዕምኑ እንድ ልማዱ ሊያስቅድስ ሲገባ፣ ከድሮው በተለየ ድምጽ የዕለቱ ቀዳሽ ጎርናና እንግዳ ድምጽ ሰማ። አቡን አልነበሩም። “እንግዲህ እንግዳ ይሆናሉ” ብለን ተዝናንተን ጸሎተ ሥርዓቱን ተከታትለን አበቃን። እንግዳው አሳርገውና ባርከው ወደቤት ይሸኙናል ብለን ስንጠብቅ አንድ ብጣሽ ወረቀት ከኪሳቸው አውጥተው አጠገባቸው ለነበረው ሊቀ ዲያቆን ሰጥተው አንብብ ብለው አዘዙት። በአጭሩ፣ “የሾምኳቸው ወኪሌ፣ ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ገብረአማኑዔል እኒህ ናቸው። ያውላችሁ፣ ተቀበሏቸው። የቤተክርስቲያኗን ንብረት አስረክቡአቸው፣” የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ነበር ከታጋይ ጳውሎስ፣ በአዲስ አበባው ሲኖዶስ በኰል የመጣ ደብዳቤ ተብሎ የተነበበልን። ጉድ እኮ ነው ጎበዝ! ደብዳቤው ተነቦ ሲያልቅ፣ ቀሲስ ብርሀኑ ቁመው “እንግዲህ ይኸውና ከኢትዮጵያ ካህን መጥቶልናል። ስሙአቸው። ለአባ ዮሐንስ የሰጣችሁትን ክብር እና አመኔታ አትንፈጉአቸው። እኔም እዚችው እንደበፊቱ ቁሜ አገለግላለሁ።” አሉን። ነገሩ አላማረንም። ጉምጉምታ በዛ። የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት፣ “አሁን ጊዜው የሱባዔ ጊዜ ነው። ከፋሲካ በኋላ የሚሆነውን እናደርጋለን፡” ብለው ሕዝቡን አረጋግተው ነገሩን ዘጉት። ወደየቤታችን ሄድን።

ትንሳዔ ደረሰ። የፋሲካ አጥቢያ፣ ገና ከመምሸቱ 12 ሰዓት ሳይሆን ግሪን ፓርክ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶኦክስ ቤተክርያን ሰው በሰው ሆነ። ያከፈሉም ነበሩ። እንዲያው ስታስቡት፣ ሕዝቡ ፋሲካ ፋሲካ ላይ እንደ ገብረ ጉንዳን ከየት ነው የሚፈልቀው? ደግሞ ታይቶ የማይታወቅ የአበሻ ልብስ የሚለበሰው ያን ቀን ነው። አቤት ሴቶቹ ማማራቸው! ግርማ ሞገሳቸው! ነጭ በነጭ የለበሱ ያገራችን ወይዛዝርትና መኳንንት፣ ስፍራውን አጥለቅልቀው የመላዕክት ጉባዔ አስመሰሉት። ቦታ ሞልቶ ሰው የሚቀመጠበት ጠፋ። በጊዜ ቦታ ቦታ የያዝን ሰዎች እየተጠጋጋን ሰው በሰው ላይ ተቀምጠ ሥነ-ሥርዓቱ ተጀመረ። ተገባደደ። መነሳቱ የማይቀር ነበርና ጌታ ክርስቶስ ተነሳ። “ክርስቶስ ተንስአ ሙታን። በዐብይ ሀይል ወሥልጣን። አሰሮ ለሰይጣን። አጋዞ ለአዳም፣ እምይዜጸ ኮነ ፍሰሐ ወሰላም!!” እያልን እልል ተባለ። ስለክርስቶስ ትንሳዔ ትንሽ ትምህርት ተምረን ተባርክን ወደየቤታችን እንሄዳለን ብለን በጉጉት ስንጠብቅ እንግዳችን፣  የታጋይ ጳውሎሱ መልዕክተኛ፣ መድረኩን ያዙትና የስድብ ናዳቸውን አወረዱብን። ግራ ተጋባን። “ምን አጠፋን? በስደት አገር እንኳን ሀይማኖታችንን ሳንለቅ፣ ወግ ማዕረጋችንን ሳንተው፣ ባህላችንን ይዘን በመቆየታችን መመስገን ሲገባን እኚህ አባት ምን አስቀይመናቸው ነው እንዲህ አብጠልጥለው የሚያዋርዱን” የሚሉ ምዕምናን በዙ። አሁንም የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት፣ መድረኩን ወስደው “ሰዓቱ የመንፈሳዊ፣ የደስታ፣ የጌታችን የክርስቶስ የትንሳዔ ሰዓት ነውና፣ ነገሩን ቀስ ብለን እንነጋገርበታለን፣ በሰላም ወደየቤታችሁ ሂዱ” ብለው አሰናበቱን። ያቺ ተአምረኛ ሌሊት በዚያ አለፈች። ምን ይቀጥል ይሆን?

ምዕምኑ የበዓሉን ሳምንት ዘመድ አዝማድን እየጠየቀ፣ እንኳን አደረስህ፣ አደረስሽ፣ አደረሳችሁ እየተባብለ አሳለፈው። ዳግማዊ ትንሳዔ ደረሰ። ሁላችንም ያለችንን አጣጥበንም ይኹን አዲስ ለብሰን፣ አምረን፣ ለጌታ ተሽቀርቀረን፣ ወደ ቤተክርስቲያን ከየአቅጣጫው ጎርፍን። ግሪን ፓርክ ስንደርስ፣ ያልጠበቅነው ጉድ ፈላብን። ቤተክርሲቲያናችን ተቆልፋብን፣ ቁልፏ ተቀይሮብን፣ ተዘግታብን፣ ታሽጋብን ጠበቀችን። ምን ዓይነት የክርስትና ዕምነት ተከታይ ነው ማርያምን በዚያ መልኩ ድፍሮአት የሚዘጋት? ማን አሸገው? ማን ቁልፏን ቀየረ? ጥያቄ በጥያቄ ሕዝቡ ተተረማመሰ። ዞር ብለን ስናይ፣ ነባሩ ካህንና እዚያችው ተምረው ያደጉ፣ ዲያቆናት ብቻ ተገኙ። አዲሱ ሊቀ ካህን ብርሽ ግን በአካባቢው ሽታቸውም አልነበረም። ማንም ሰው ግን፣ ካህን ቤተመቅደስን

በምዕምኑ ላይ ዘግቶ ይጠፋል ብሎ የገመተ አልነበረም። እንዴት ተደርጎ ሊታሰብ! ሕዝቡ በረቱ እንደተናደበት የኩብት መንጋ ሜዳ ላይ ፈሰሰ። የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት ላይ ታች ተሯሩጡ። ቁልፉን የቀየሩት እና አሸገው ከቦታው የተሰወሩት፣ ካድሬው ሊቀ ካህናት ብርሀኑ ገብረአማኑዔልና ተባባሪአቸው እነሙሉጌታ አሥራተ ሁነው ተገኙ። ወይ አንተ አምላክ! ወይ አንተ ክርስቶስ! አሁንም ሙሉጌታ አሥራተ? አንዴ ኮትልኮ፣ ሌላ ጊዜ የጸነጠጠ ከሀዲ፣ አሁንም አልለቀቀንም!

ቤተ ክርስቲያኗን ያለሕግ ፈቃድ ሰብሮ መግባት ስለማይቻል፣ ጉዳዩን ለሰበካ ጉባዔው አመራር ተተን ወደ ግሪን ፓርክ መናፈሻ ሜዳ ተመምን። ቀሲስ ብርሀኑና ዲያቆናቱ በአውላላ ሜዳ ላይ ቁመው ጸሎተ ቡራኬውን ማካሄድ ሲጀምሩ፣ ዝናብ መዝንብ ጀመረ። ዝናቡ የሚገርም ዓይነት ዝናብ ነበር። የዝናቡ ውሀ ለብ ያለ እና ከለላ ፍለጋ የሚያስሮጥ አልነበረም። አንዳንዶቹ ሴቶች ሲያልቅሱ ነበር። ብዙዎቻችን በዕውቀት ሳይሆን በዕምነት ብቻ ከጌታ እየሱስ ክርስቶስ ጋር የተጣበቀነው ተራ አማኞች፣ ያችን ለብ ያለች ዝናብ "የጌታ እምባ" አልናት። አልተከፋንም። ጌታ ይመስገን። በደሙ እንደታጠብን ሁሉ ያቺን ዕለትም እንዲሁ በእንባው እንደገና እንደተጠመቅን ወሰድነው። ለማንኛውም በክርስቶስ ማመን ጽናትን ይሰጣል። እንደዚያ ሜዳ ላይ ፈሰንም ቢሆን፣ ዕምነታችን አልተሸረሸረችም። እንዲያውም ጸንተን ከጭንቅ ወጣን። የማርያምን ተአምር መጠበቁን ተያያዝነው። የጌታ እናት አትሸንፍም።

የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት በሚያስደንቅ ፍጥነት፣ መከፈል ያለበትን ገንዘብ ከፍለው፣ ጠበቃ ይዘው፣ የሕግ መንገድን ተከትለው፣ ሕገወጦች የወያኔ መልዕክተኞች ያሸጓትን እሽግ ሰብረው፣ ቁልፏን በጣጥሰው ጥለው፣ የማይሰበር ቁልፍ ተክተው ቤተክርስቲያናችንን ተረከቧት። ሌላ እሁድ መጣ። ምዕምናን ቤተ ክርስቲያናችንን ከክፉ አውሬዎች በማስጣላችን፣ ደስ አለን። እግዚአብሔርን አመሰገነው። አገልግሎቱ ቀጠለ። ቤቱ በጌታ ልጆች ሙልት አለ። መህል ቅዳሴ ላይ እራሳችንን ለጸሎት ዝቅ ዝቅ አደረግን። በንስሀ ሰመመን ሰምጠን እየለን ከወደበሩ አካባቢ እንቅስቃሴና የሰው ድምጽ ሰማን። ምንም ሳንረበሽ የንስሀውን ጸሎት አበቃንና ቀና ቀና አልን። ፖሊሶች እና የሰበካ ጉባዔ አመራር አባላት ነበሩ እመግቢያው ላይ ቁመው የሚጨቃጨቁት። "ውሾች ይዘን እንገባለን"፣ "አትገቡም" ነበር የሚባባሉት። አንድ ፖሊስ ወደ ውስጥ ገብቶ ጸጥ-እርጭ ብሎ የሚጸልየውን ሕዝብ አየት አርጎ ደንግጦ በርግጎ ወጣ። ነገሩን በኋላ ላይ እንደተረዳነው፣ "ልዑል ሙሉጌታ (Prince Mulugeta) አሥራተ ነኝ" ባይ ቦዞ፣ ለፖሊሶች ደውሎ፣ "ግሪን ፓርክ የሚገኘው ቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ ረብሻ ተነስቶ፣ ሰዎቹ እየተደባደቡ ሥፍራው ደም በደም ተጥለቅልቋልና ቶሎ ድረሱ" ብሎአቸው፣ እንሱም አደጋውን ለመቅጨት፣ አንዷት ሰኮንድ እንኳ ሳያጠፉ፣ ከየአቅጣጫው ከተማዋን ጡሩንባ፣ በጡሩንባ እየረብሹ፣ ነብስ ለማዳን እየከነፉ ከቸች አሉ። የሰበካ ጉባዔው አመራር አባላትም፣ ዲይብሎስ መምጫው በየት በኵል እንደሆነ አይታወቅምና ብለው፣ በአራቱም ማዕዘን በተጠንቀቅ ቁመው በማስቀደስ ላይ ስለነበሩ፣ ፖሊሶቹ ውሾችን ይዘው ሲደርሱ እንዳይገቡ አገዱአቸው። ምንም እንዳልተፈጠርም፣ አስረዱአቸው። ከፈለጉም፣ ያለውሾቹ ገብተውም እንዲመለከቱ ጋብዙአቸው። ፖሊሶቹ በደረሱ ከ5 ዲቂቃ በኋላ ሙሉጌታ ተንኰሉ ቁና-ቁና እየተነፈሰና እያለከለከ ሥፍራው ደረሰ። የሰበካ ጉባዔው አመራር አባላት፣ "ሙሉጌታ አስራተ ነኝ ብሎ የደወለላቸው ግልሰብ ያውላቸሁ" ብለው ጠቆሙአቸው። ፖሊሶቹ ሙሉጌታንና ካድሬው ካህን ከበቡ። ወደጎን ወሰደው አነጋገሩአቸው። ነገሩ እንዲህ ነበር። ፖሊሶች ቀደምው ደርሰው ዕቅዳቸው ከሸፈ ኢንጂ፣ ተንኰላቸውማ ሰይጣናዊ ዕቅድ ነበር። ትራፊክ ይዞአቸው ሲገተሩ፣ ፖሊስ ቀድሞአቸው ሥፍራው ደረሰ። መድረሱንም ሲረዱ፣ ዕጢአቸው ድብ-ዱብ አለች። እነሱ አቅደውት የነበረው ሸር፣ ድሩዬ ይዘው ከፖሊስ ቀደመው ደርሰው ግርግር ሊያስነሱ፣ ከሳሹ የደብሩ አስተዳዳሪ ነኝ ባዩ፣ ሊቀ ካኅናት ብርሀኑ ገብረአማኑኤል ሊሆኑ፣ ፖሊሶች ደርሰው ካዳኑአቸው በኋላ፣ ቤተክርስቲያኗንም ክነንብረቷ ለታጋይ ጳውሎስ አሽከሮች ሊያስረክቡ፣ እኛ ግን ዘብጥያ ልንወርድ ነበር። ግን አልሆነላቸውም። ጠብ ከማንሳታቸው በፊት ፖሊስ ቀደሞ ደርሶ የሰላምና የፍቅር ሰዎች እንደሆንን ተረዱልን። ለጠብ አጫሪነት የመጡት እራሳቸው ፖሊስ ጠሪዎቹ ሁነው ተገኙ። "ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው!" ይባል የለ? ሙሉጌታ የሚይዘውን የሚጨብጠውን አጣ። ፖሊሶች ሁለተኛ በውሸት እንዳይጠራቸው አስጠቀቁት። ድራሹ ከዚያ ጠፋ።



እኒያ የጌታን በጎች ሜዳ ላይ ያፈሰሱት ካህን ተብዬ “ቤተክርስቲያን-አሻጊ” ካድሬ፣ ከዚያች ቀን በኋላ፣ በየትኛው ወኔያቸው እዚያች ድርሽ ሊሉ! እንደውጧት ቀሩ። እየተራገሙም ወደ ኢትዮጵያ ብርር ብለው ተመለሱ። የሰይጣን አሽክረን እርግማን የሚሰማ ሰይጣን ብቻ ነው። ጻድቃን አይፈሩም። አምላክ ያቆመላቸው ጠባቂ መላዕክት ከማንኛውም ተወረዋሪ ፍልጻ ያደናቸዋል። ምዕምኑ ልባችናን ሞልተን የሚመጣውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመጋፈጥ ተዘጋጀን።

# መለስተኛ የሰላም ጊዜ

የግሪን ፓርኩ፣ የቤተክርስቲያናችን ሕንጻ ንብረትነቱ የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ነበር። ሥራ አቁሞ በመበስበስ ላይ የነበረውን (derelict) ሕንጻ፣ ኢትዮጵያውያን ተከራየተው፣ አዲሰውት፣ እንደገና አንጾውት፣ ካህናቱ ባርከውት ለቁምነገር ተቀደሰ። ታጋይ ጳውሎስ ለካንተበሪው ሊቀ ጳጳስ ክብደቱ ብቻ እጅ የሚገንጥል የወርቅ መስቀል ሸልመዋቸው ስለነበር፣ ወዳጄ ነው ብለው ይተማመኑባቸው ነበር። ታዲያ “እዚያ ቤተክርስቲያን የሚያስቀድሱት የኔ ተቃዋሚዎች ናቸውና አውጥተህ ጣላቸው” የሚል የወደጅነት ደብዳቤ እንደጻፋላቸው ደረስንበት። ቢሆንም ምንም ቢሆን አንግሊካኖች እንደኛው የክርስቶስ ቤተሰቦች ነበሩና አውጥተው ሜዳ ሊጥሉን አልፈለጉም። ብዙ ታግሰውናል። እግዚአብሔር ይባርካችው። ቀስ ብለው “ቤተክርስቲያን ፈልጋቸው ልቀቁ” አሉን።

“ታጋይ ጳውሎስ ደግመው በየት በኵል ይመጡብን ይሆን?” ብለን በመስጋት ሌት ተቀን መጠባበቅ ገባን። ቅደስት ማርያም መቸም ተአምሯ ተወስቶ አያልቅምና የራሷን የቤት ሥራ ሠራች። ተበራታተን በእግራችን ተጠናክረን እስክንቆም ድረስ፣ ታቦተ ጽዮን እራሷ፣ ከትግራይ ልጇቿን አስነስታ፣ ታጋይ ጳውሎስን ገፍታ ጥግ አስያዘቻቸው። የትግራይ ክርስቲያን ወገኖቻችን እኚህን ምንም ዓይነት የክርስትና ምግባር ይቅርና ሽታውም በአጥገባቸው ያላለፈዉ ፓትርያርክ ክፉ ሥራ እዚያም ተንሰራፍቶ ኑሮ፣ የሕዝቡ ቁጣ ገንፍሎ፣ ተቃውሞ ተነሳባቸው። ታጋይ ጳውሎስ፣ ትግራይ የተንቀለቀለባችውን ቋያ እሳት ሊያጠፉ፣ ተፍ ተፍ ሲሉ፣ የለንደን ክርስቲያኖች ለጊዜውም ቢሆን ለቀቅ አደረጉን። ተነፈስን። የትግራይን ክርቲያን ሕዝብ አስቀየሙ ማለት ደግሞ፣ ፓትርያርኩ የብትርክናቸውን በትር እስክትሰበር የሚያሰጋ አደጋ ስለነብር የለንደንን ነገር ለጊዘው ተወት ለማድረግ ተገደዱና ሥልጣናቸውን ጠበቅ ለማድረግ እዚያው ሌትና ቀን በሥራ ተጠመዱ። ተመስገን! ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለሚቀጥሉት ሰባት ዓመታት መለስተኛ ሰላም ሰፈነልን።

# አዲስ ቤተክርስቲያን



እንዲያ እንዲያ እያልን ስንተሻሽ በፈረንጆቹ አቆጣጠር እስክ 2001 ዓ ም እዚያው ግሪን ፓርክ ቆየን። የታጋይ ጳውሎስ ምልጃ አንግሊካን ላይ እየጠንከረ መጣ መሰል፣ ባለንብረቶቹ “እስካሁን ጡብቀናችሁአል። ሕንጻውን ልቀቁልን” የሚል ግፊታቸው እየጠነከረ መጣ። የአባ ጳውሎስ ሰዎች ቤትክርስቲያኗ ከካቶሊኮች ቤተክርስቲያን ጋር ተዳብላ እንድትገለገል ቦታ እንዳገኙልን ይወተውቱን ገቡ። የኛ ሥርዐት ከሌሎቹ ይለያል፣ ታቦት አለን፣ እንዴት አድርገን ከሌሎች ተዳብለን እንጸልይ በማለት ተጋፈጥናቸው። አሁንም የሰበካው ጉባዔ አመራር ሌት ተቀን መሥራት ጀመረ። በምሥራቅም በምዕራብም፣ በሰሜንም በደቡብም ቤተክርስቲያን ፍለጋ ተሰማራን። መጨረሻ ላይ፣ እግዚአብሔር ይመስገን ምን የመሰለ የተንጣለለ የቅዱስ ፍሊጶስ ቤተክርስቲያን ተገኘልን። ለነገሩስ፣ የሐዋርያት ሥር ምዕራፍ 8 ከቁጥር 26 — 40 እንደሚያስተምረን፣ ቅዱስ ፍሊጶስም አልነበር የመጀመሪያውን ኢትዮጵያዊ ያጠመቀው? በጊዜው የንግስታችንን የገንዘብ ቤት ሃላፊ የነበረውን ጃንደረባ፣ የሚያነበው መጽሐፍ ግራ አጋብቶት ፍቺውን ፍለጋ ሲያዝን ጋዛ ውስጥ አግኝቶ፣ ምስጢሩን ገልጠለት፣ አንድ ወንዝ ዳር ወስዶት በአብ በወልድ በመንፈስት ቅዱስ ስም አሳምኖ ክርስቲያን ያደረገው?

አሁንም ቅዱስ ፍሊጶስ የኢትዮጵያን ልጆች እንደገና ደብረጽዮን ቅደስት ማርያምን ታቦት ይዘው ማሳደሪያ አጥተው እንግሊዝ አገር ቴምስ ወንዝ ዳር እረኛ እንዳጡ በጎች ሲንከራተቱ አግኝቶ አዘነላቸው። በሰሙ የሚጠራውን ቤቱን ለእናታችን ልቅድስት ማርያም ስም መጠሪያ፣ ለልጆቿ መሰብሰቢያ ለቀቀላት። በሆታና በዕልልታ ታቦቱ ከግሪን ፓርክ ውጥቶ ወድ ባተርሲ ተጉዞ ቅዱስ ፍሊጶስ በተክርስቲያን አረፈ። በጊዜ ሂደትም የቅዱስ ፍሊጶስ ቤትክርስቲያንም የአሁኗ ርዕሰ አድባራት ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ለመባል በቃ።



ይኸም ሆኖ እርሰበርስ ማባላቱ ላይ ተጠናክሮ፣ አንድ ጊዜ የቤተክርስቲያኑ አስተዳዳሪ በነበሩት በቀሲስ ብርሀኑ ላይ የተወሰኑት ካህናት ተነሱባቸው። ቀሲስ ብርሀኑም ነገር ዓለሙ ስልችት ብሎአቸው፣ ለተወሰነ ጊዜ ቤተሰባቸውን፣ ልጆቻቸውን ከሁሉም ከሁሉም እኛን የመንፈስ ልጆቻቸውን ትተው ወደ ሶስተኛ አገር ተሰደዱ።

ይኸ ሁሉ የኢትዮጵያ ሰደተኛው የክርስቶስ ቤተሰብ እንዲህ ዓይነቱ መጉላላትና፣ የታጋይ ጳውሎስ ዘመቻ ጥቃት ሰለባ ሊሆን የቻለው የራሱ የሆነ የቤተክርስቲያን ሕንጻ ስላልነበረው መሆኑን በመረዳት በቁጭት ተነሳስቶ የቤተክርስቲያን ሕንጻ ግዢ ገንዘብ አሰባሳቢ ኮሚቴ አቋቁሞ እልህ አስጨራሹን ትግል ተያያዘው። በዚህ መሀል፣ ብዙ ጭቅጭቆች ተነስተው ነበር። የታጋይ ጳውሎስ ሰዎች የተሰበሰበውን ገንዘብ ለመንጠቅ ያልሸረቡት ሸር፣ ያልገመዱት ተንኰል አልነበሩም። የሰበካ ጉባዔው፣ ካህናቱና ሕዝቡ ነቅቶ ስለሚጠብቅ አንዳችም መፈናፈኛ መንገድ አጡ። እንደማይታለፍ የለምና ያንንም አለፍነው። በዚህ አኳኋን እያለን የተከራየነውን ሕንጻ ባለቤቶች አያያዛችንን፣ የዕምነታችንን ጽኑነት አይተው፣ ከፈለጋችሁ ሕንጻውን ግዙት አሉን። ትልቅ ዜና ነበር። ግን በምናችን! ባንክ ቤት ሄድን። ብድር አጣን። ያለን ገንዘብ እንኳን ያንን ሕንጻ ከነቪካሬጁ ሊያስገዛን አንድ አሥርኛውንም አይሸፍንልም። እንዴት እናድርግ ተባለ። ይኸንን እልህ አስጨራሽ ልንወጣው ገንዘብ የማሰባሰቡን ጥረት ተያያዝነው። የሚያስፈልገን ከ£1 800 000 የእንግሊዝ ፓወንድ በላይ ነበር። ማርያም ታውቃለች በማለት የቻለነውን ሁሉ ማድረግ ጀመርን።

## አባ ሙሴ



በዚህ መሀል አንድ አቡነ ሙሴ የሚባሉ አባት አንድ ቀን ሰተት ብለው ቤተክርስቲያኗ ገቡ። እንግዳ መቀበል ልማዳቸው የሆነው የቤተክርስቲያናችን ካህናት ብድግ ብድግ ብለው ወደ መቅደሱ መሯቸው። ያችን ዕለት አቡነ ሙሴ ሥርዓት ቅዳሴውን መሩት። ኋላ ኋላ ላይ ማን እንደሆኑ ስናጠያይቅ ለሕክምና ብለው የመጡ፣ ከታጋይ ጳውሎስ ጋር በጣም ጥለኞች እንደሆኑ ከልክ በላይ ተጋኖ ተወራልን። ሆሆይ! ተዲያ ለምን የደብሯ አስተዳዳሪ አይሆኑም እስከማለት ተደረሰ። ለማንኛው እሁድ እሁድና በየበዓላቱ እየመጡ እየቀደሱና እያስቀደሱ ብዙ ጊዜ ቆዮ። በግል ያገኙአቸው ሲናገሩ፣ በሄዱበት ታጋይ ጳውሎስን እንዳወገዙና ስለሳቸው ክፉ እየተናገሩ፣ እያጋለጡአቸው ነው ተባለ። የደብረጽዮን ቤተኛም ሆኑ። ቀስ በቀስም ታመሙ የተባሉትአቡን ደኅና ሁነው ከመቀደስም አልፈው ይሰብኩ ጀመር። ጥሩ!

ምርጫ 97 (በፈረንጆች 2005) በኢዮጵያ ምድር ተካሄደ። ወያኔ ሲሸነፍ፣ ሰኔ ወር ላይ በአጋዚ በአዳፍኔና በመትረየስ ወጣቶችን በአዲስ አበባና በአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች መንገዶች ላይ በጭካኔ ረፈረፈ። ከወያኔ ገዳዮች ሸሽተው ቤተክርስቲያን ግቢ የገቡትን ወጣቶች ታጋይ ጳውሎስ ሰዎቻቸውን አዘው  አሳልፈው ለገዳዮቻቸው እንዳስረከቡ ዜናው ተሰማ። ሕዝቡ አዘነ። ምዕምኑም ቤተክርስትያኗን ለነዚያ ለሞቱት ሰዎች ጸሎት እንዲደረግላቸው ጠየቀ። ካህናቱም በነገሩ በጣም አዝነው ነበርና በመሀላቸው ተወያይተውበት ሥርዓተ ጸሎቱን አንድ ሰንበት ዕለት አካሄዱት። የሞቱትን የወንድሞችና እህቶች ፎቶግራፎች እየታዩ ገለጻም ካህናቱ አደረጉ። የታጋይ ጳውሎስ "ቀንደኛ ጠላት ነኝ" ባዩ አባ ሙሴ ሆዬ ከተቀመጡበት እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው አፈፍ ብለው ብድግ አሉ። እንደ ቀስት እየተስፈነጠሩ ተቆጡ። "ማን ገድሎ ማን ሙቶ ነው ፍትሀት የሚድረገው" ብለው ያዙኝ ልቀቁኝ አሉ። ግራ ተጋባን! ምንድነው ነገሩ! ከትግራይ ስለመጡ ብቻ የወያኔን ግድያ ማጽደቃቸው ነው? "ሀይ ሀይ" ተብለን ነገሩ ተድበስብሶ ያን ቀን አለፈ።

## አሳፋሪው፣ የታጋይ ጳውሎስ ሌላ ሙከራና የአባ ሙሴ ግዝት።



የቅዱስ ፍሊጶስን ቤተክርስቲያን ሕንጻ ገዝተን የራሳችን ለማድረግ ሩጫው ቀጠለ። ሻጮቹም ረድተውን፣ የምንገዛበትን መንገድ ሲያመቻቹልን፣ የውስጥ ቦርቧሪዎች ዜናውን አዲስ አበባ አድርሰውት ታጋዩ የወያኔ ፓትርያርክ ቢሮ ደረሰ። ሰይጣን ጆሮአቸው ውስጥ አንድ የተንኰል ሥራ እንዲሠሩ ሹክ አለባቸው። እንደምንም የሻጮቹን አድራሻ አግኝተው፣ "እኔ የማላውቃቸው፣ ከኔ ትዕዛዝ ውጭ ያፈነገጡ ክርስቲያኖች ናቸውና፣ ለነሱ እንጻውን እንዳትሸጡት" የሚል ምስጢራዊ ደብዳቤ ጻፉላቸው። "የኔ ሹም፣ ሮም ያሉት አቡነ ዮሠፍ ናቸውና፣ እሳቸው የማያውቁትን ምንም ዓይነት ሕጋዊ ስምምነት እንዳተፈርሙ የምትል፤ ልክኳን የማታቅ ትዕዛዝ ከላይ በተመለከተው ደብዳቤ ከአዲስ አበባ ከፓትርያርኩ ቢሮ ከተፍ አለች! ምን?

ሻጮቹ እንዲህ ዓይነት ደብዳቤ ከአፍሪካ ታዳጊ አገር ሲደርሳቸው ገረማቸው። ይኸ ነጻ አገር ነው። በነጻ ገቢያ በገዥውና በሻጩ ግለሰቦች ወይ ተቋም እንጂ፣ ይኸን ለዚህ ሸጥ፣ ይኸን ለዚህ አትሸጥ የሚል ትዕዛዝ የሚሰጥ፣ እንኳን አንድ አምባገነን የነገሠባት የታዳጊ አገር፣ ያውም የሀያማኖት መሪ ነኝ ባይ ይቅርና፣ የራሷ፣ የሀገሪቱም የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስቴርም ቢሆን ግለሶቦች መሀል ገብቶ እንዲህ ዓይነቷን ድፍረት አይሞክራትም። ለማንኛውም ሻጮቹ ወኪሎቻችንን ጠርተው፣ ድብዳቤውን አሳይተው፣ "Who is this chap?" ብለው ጠይቁ። "ማነው ይኸ ደፋር ወጠጤ?" እንደማለት ነው። ነገሩ አሳፋሪ ነው። እንዴት ተብሎ ማስረዳት ይቻላል?

ለማንኛውም በሚቀጥለው ሰንበት የሰበካው ጉባዔ መሪዎች ታጋይ ጳውሎስ የጻፉትን አሳፋሪ ደብዳቤ አነበቡልን። የምዕምናን ቁጣ ገነፈል። ቀጥለዉም፣ የካህናትና የሰበካው ጥምር ጉባዔ አመራር ያሳለፈውን ውሳኔ ነገሩን። ለብዙዎቻቻን የምሥራች ዜና፣ ነበር። እልልታውና ጭብጨባው ውሳኔአቸው ትክክለኛ እንደሆነ አረጋገጠላቸው። በተለይ ለእኛ፣ ቤትክርሲያኗን ውስጥ ጸንተን ለኖርነው፣ እዚያች ተአምረኛ ደብር ውስጥ በትዕግስት ለጠበቅናት ልዩ የምሥራች ነበር። የራሳችን ቤተክርስቲያን እንዳዮኖረን እንቅፋት ለመሆን የሞከሩት ታጋይ ጳውሎስን ከዚያች ቀን ጀምሮ "ብጹዕ ወቅዱስ ተብለው መጠራታቸውም እስክነአካቴው ቀረባቸው። አባ ሙሴ እንደገና እሳት ለብሰው እሳት ጎርሰው ተስፈንጥረው ከተቀመጡበት ተንሱና መነጋገሪያውን ነጠቁ! ደብዳቤውን ወዳነበቡት ወጣት ካህን ዞር ብለው፣ "አንተ ነህ ጳውሎስን እንደዚያ መናገር የምትችለው?! አንት አጉል ደፋር! አንተ ማን ነህ!?" በማለት አምቧረቁ። ሰው ሁሉ ከው ብሎ ደርቆ ቀረ። በካህኑ እንዳፈጠጡም! "ገዝቼሀለሁ! ሁለተኛ እንዳትቀድስ" ብለው እንደ ፍርደ ገምድል አለቆቻቸው ፈረዱ። ሕዝቡ ጨኸባቸው። መነጋገሪያውን አንድ ዲያቆን ነጠቃቸው። "እሳቸው፣ አስተዳዳሪ አይደሉ። ተቀጣሪም አይደሉ። ለመሆኑ ማናቸው ከመሬት ተነስተው የሚገዝቱ" ተባለ። እንደነገሩ ሌሎቹ ካህናቱ ባረኩንና አሰናበቱን። እያረርን ወደየቤታችን ሄድን። ወይ ፈተና! ወይ መሰናከል!

ያ ከአንድ አባት የማይጠበቅ አብግን የአቡነ ሙሴ ድርጊት እንዲሁ መታለፍ እንዳልነበርበት ብዙዎቻችን አመንበት። በዚህ ነጻ አገር ዝም ብሎ ሰውን መዝለፍ ተገቢ አይደለም። አስነዋሪ ጉዳቸውን ያን ዕለት ቤተክርስቲያን ባለመምጣት ያመለጣቸውን የለንደን ነዋሪዎች እንዲሰሙአቸው ፈለግን። "ንጋት" የተባለ የሕብረተሰባችን አንድ ሬዲዮ አለ። ታዲያ የዚያ ሬዲዮ ጋዜጠኞች፣ የአቡኑን ዕብሪተኛነት ለማየት የዓይን ምስክሮች ነበሩና ቀረብ ብለው፣ "እንዲያው አባታችን፣ ይኸንን ዛሬ ከሥርዓት ውጭ ካህኑ ሲሆኑ አይተው የገዘቱበትን ሆኔታ አብዛኛው ሕዝብ እንዲያውቀው በሬዲዮናችን ያስረዱልን" በማለት በትሕትና ጠየቁአቸው። አባ ሆዬ "ዕድል አገኘሁ" አሉና ሰፍ ብለው "እንዴታ! ደስ እያለኝ" አሉ። በጎን፣ ጋዜጠኞቹ እኛን፣ በግልጽ የወያኔ ግፍ በመቃወም የምንታውቀውን ግለሰቦች፣ "የምታደርጉትን አድርጉ" አሉን። ፍቱን መድኃኒት የሆኑትን አባት፣ ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛውን አዘጋጀን። ሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው፣ የድሮ የቤተክሕነታችን ዋና ሥራ አስኪያጅ የነበሩና፣ በቤተክህነት ሥነሥራዓትም ጥልቅ ዕውቀት እንዳላቸው ያስመሰከሩ አባት ናቸው። አባ እንደፈለጉት እንዲፈነጩና፣ ለቀ መምራን አበባው ይግዛው በስልክ ጸጥ ብለው እንዲያዳምጡአቸው ተደረገ። አስመሳዩ የታጋይ ጳውሎስ "ጠላት" ነኝ ባይ ጳጳስ፣ $180^0$ (ድግሪ) አክሮባት ሠርተው ዙረው የታጋይ ጳውሎስ አንድ ቁጥር ጠበቃ ሁነው ተገኙ። እንዲህ ሲሉም ማስረዳት ጀመሩ። "ወደድንም ጠላንም፣ የቤተክህነታችን ራስ፣ አቡን ጳውሎስ ናቸው (የክርስቶስ መሆኑ ቀረና)። አቡነ ጳዎሎስን የማይቀበል ቤተክርስቲያን፣ ውጉዝ ከመአርዮስ ነው" አሉ። የመሰላቸውን ተናግረው ሲያበቁ፣ "እስቲ ስለዚህ ግዝትዎ አስተያየት ከአንድ ከሌላ የቤተክርስቲያን ምሑር እንስማ" በማለት ጋዜጠኞቹ፣ ዕድሉን ለሊቀ ማምራን አበባው ይግዛው ሰጡ። "ከሳሽ የተከሳሽን ልብ ቢያውቅ ኑሮ..." ነበር የተባለው? ሊቀ ማምራንም "ግዝት" ምን እንደሆነ፣ አንድ አባት መቼና በምን ሁኔታ ሊገዝቱ እንደሚችሉ፣ ሥልጣናቸው እስከየት እንደሆነ፣ ለኛ ለተራዎቹ በሚገባን ቋንቋ ጥርት አድረገው ረጋ ባለ አንደበት አስረዱ። ስለዚህ የታጋዩ ጳውሎስ ጠበቃ ግዝት፣ በቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት አባባል "ወፈ ግዝት" ወይም "የወፍ ግዝት" ይባላል ብለው፣ እታች አውርደዋቸው። ግዝታቸው ምንም  ሕጋዊ እንዳልሆነ አስረዱን። ያም ብቻ አልነበረም። በሊቀ ማምራን ጥልቅ ገለጻ፣ አባ ሙሴ ያለምንም ዕውቅውትና ችሎታ፣ ታጋይ ጳውሎስን ብቻ እንዲያገለግሉ ከመንገድ ተጎትተው የጸጸሱ አስመሰላቸው። ሊቀ ማምራን አበባው፣ አቡነ ሙሴን ያውቁአቸው እንደሆነም ተጠይቀው ሲያስረዱ፥ በአባ ጳውሎስ ተገፍተው እንደመጡ ሰምተው፣ ሰዎችም እንዲረዱአቸው እሳቸው ጋ አምጥተዋችው ከልብ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደቸሩአቸው፣ የጥገኝነት ጥያቄ ጉዳያቸውንም ለማስፈጸም አብረዋቸው እላይ እታች እንደተንከራተቱ፣ እና በትርጉም እንደረዱአቸው፣ አስረዱ። ቀጥለውም፣ አባ ጳውሎስን በየሄዱበት ሲዘልፉ፣ ስድባቸውን ለመተርጎም እንደተቸገሩና ብዙውን ጊዜ ግምት ላይ እንዳይወድቁ በመስጋት፣ እያለሳለሱ

እንደተረጎሙላቸው አስረድተው፣ እንዴት አድረገው እንዲህ ተገልብጠው አሁን የታጋይ ጳውሎስ ጠበቃ መሆን እንደቻሉ ሊገባቸው ያልቻለ ስውር ምስጢር መሆኑን አፈንድተው አረፉት። ሰው ጉድ አለ።

አባ ሙሴ ለተወሰነ ጊዜ ከቤተ ክርስትያኗ ገለል ብለው ቆይተው አንድ እሁድ ብቅ አሉ። አንዳንዱ ምዕምን ቀጣው ነደበት ጫክ እያለ ይናገራቸው ነበር። የቅዳሴው ሥነ-ሥርዓት እንዳለቀ፣ አሁን ለመናገር በትሕትና መነጋገሪያውን ለመቀበል ጠየቁ። አንድ ዲያቆን አቀበላቸው። ባለፈው ጊዜ ተሳስተው በመቆጣታቸው እንዳዘኑና፣ አሁን ነገሩ እንደበረደላቸው፣ ብዙዎቻችንንም እንዳሳዘኑ ተናግረው፣ ያወገዙትን ወጣት ካህን ይቀርታ እንዳደረጉለትና ግዝታችውን እንዳነሱለት ተናገሩ። የታጋይ ጳውሎስ ምንደኞች ቢያጨበጭቡም፣ አብዛኛው ከቁብም አልቆጠረውን። እንዲያውም አንድ ፊትለፊት ቁሞ የነበረ ወንድም፣ በጣም ተናደ ኃይለ ቃል ይናገራቸው ነበር። ታዲያ እንደምንም ሕዝቡ ከተረጋጋ በኋላ፣ ጎሮሮአቸውን ጠራርገው፣ እነሆ አዲስ ቤተክርስቲያን ከደብረጽዩን ቅደስት ማርያም ቤተክርስቲያን ገንጥለው ስለመሠረቱ፣ እዚያም እየሄድን እንድናስቀድስ ጋብዘውን ከመድረኩ ወረዱ።

በግለፍተኝነት ተነሳስተው፣ የታጋይ ጳውሎስ ስም ተንስቶ ያለመጸለዩ ያበገናቸው ደቂቀ ጳውሎስ ተጠራርገው፣ አቡነ ሙሴን ተከትለው ወደ አዲሱ፣ ወደሚመቻቸው ቤተክርስቲያን ቦታ ነጎዱ። ተአምረኛዋ ማርያም እኛ በምንም ዓይነት ልንገላገላቸው ያልቻልናቸውን የውስጥ ቦርቧሪዎች በገዛ ፈቃዳቸው ከመሀላችን እንደፈየል መንጋ ነድታ ጠራርጋ አስወጣቻቸው! ተምስገን! ተመስገን እንጂ ምን ይሏል! ግልግል!

ይኸ የአባ ተንኰል፣ ቤተክርስቲያኗን የሚገነጣጥል ቢሆንም (በኋላ ላይ አባ እንጦስ ትግርኛ ተናጋሪውን ከሌላው ለይተው ለሁለት ከፍለውታል)፣ እኛን መለየታቸው ቢያሳዝነንም እነሱን አስደስቶአቸዋል።

# ዛሬስ አባ ሙሴ የት ናቸው?

አባ ሙሴ ደቂቀ ጳውሎስን መርተው ወጥተው ሥላሴን ከመሠረቱላቸው በኋላ በቀጥታ የሄዱት ወደ አዲስ አበባ ነበር። ድሮውንም የጥገኝነት ጥያቄ ያቀረቡት፣ ስደተኛ መስለው እመሀላችን ገብተው፣ ደብረጽዮንን ማርከው ለታጋይ ጳውሎስ ግድያ ሊጥሉላቸው ነበር የመጡት። የጥገኝነት ጥያቄአቸው ውድቅ ሲሆንባቸው ለመመልስ የግድ ሆነባቸው። እንደሰማነው ከሆነ፣ ደቂቀ ጳዎሎስን ከማርያም መውጣት ታጋይ ጳውሎስን አላስደሰተም። ጳጳስ ለአዲሲቱ ሥላሴ እንዲልኩ ሲጠየቁ፣ “እዚያው ማርያም ሆናችው ከውስጥ ተጠናክራችሁ መያዝ ነበረባችሁ እንጂ እንዴት ጥላችሁላቸው ትሄዳላችሁ?” በማለት እንደተቆጡአቸው ሰምተናል። ለማኛውም አባ እንጦስ የተባሉ አቡን ወደ ለንደን ተልከው ወደ ማርያም ሊሚጡ ሲሞክሩ መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሲነገሩአቸው፣ አሻፈረኝ በማለታቸውና ባለመቀበላቸው፣ እዚያው አባ ሙሴ ባዘጋጁላቸው ለመወሰን ተገደዱ።

ስለታጋዩ ጳውሎስ ታማኝ አገልጋይ አሁንም ትንሽ እንበል። አባ ሙሴ ለንደን መጥተው ርዕስ አድባራት ደብረ ጽዩን ማርያምን ለታጋይ ጳውሎስ መማረክ ቢያቅታቸውም፣ ሲኖዶሱ ውስጥ ታጋዩን ፓትርያርክ የሚቀናቀኑ አባቶች ስለተነሱባቸው ያንን እሳት ለማጥፋት ወደዚያው ተመልሰው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ሲኖዶሱ፣ ግንቦት 2002 ላይ የታጋዩን ፓትርያርክ ስልጣን ለመገደብ ውሳኔ እንዳስተላለፈ በኢ. ኤም ኤፍ (EMF)[1] እንዲሁም ደጀሰላም[2] በተባሉ ድህረ-ገጾችና ከአገር ቤት ከሚመጡ ጋዜጦች እንዲሁም ከቪ ኦ ኤ ሬዲዮ ሰምተናል። ታዳያ በነዚህ የዜና ማሠራጫዎች እንደተረዳነው የፓትሪርኩን ሥልጣን ለማትረፍኝ ከቻሉት አራት ሰዎች መሐል አንዱ አባ ሙሴ ነበሩ[3]። ሌላዋ ቀኝ እጃቸው፣ ሸጉጥ ታጥቃ አባቶችን “እንጭርሳችሁአለን” እያለች ታስፈራራ የነበርች የድሮዋ የአርቲስት መሀሙድ አህመድ ባለቤት የነበረች፣

---

[1] http://ethioforum.org/?p=1205

[2] http://www.dejeselam.org/2009/05/blog-post_27.html

[3] http://deje-selam.blogspot.com/2009/07/blog-post_7004.html

ወይዘሮ እጅጋየሁ በየነ የተባለች ሴት ናት። እንገድላችሁአለን ብለው በዛቱትም መሠረት፣ ቤተ ከህነቱ ግቢ ገብተው፣ በር ሰብረው አባቶችን ሊያርዱ ሲሉ፣ አንዳንድ አባቶች በጓሮ በር ሩጠው ጨኽው እንደተርፉ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ወደ አውስትራላይ ተልከውም ተመሳሳይ የመለያየት ሥራቸውን እንደፈጸሙ ሰምተናል።

# የለንደኖቹ ኢትዮጵያውያን ቆራጥ ውሳኔ

ወደ ለንደን ስንመለስ፣ የአባ ጳውሎስ ሰዎች ቤተክርስቲያናችን ከለቀቁ በኋላ፣ የተቀሩት ካህናት ተሰብስበው፣ ተወያይተው፣ ተስማምተው አንድ ቆራጥ ውሳኔ አሳለፉ። የውሳኔ ሀሳቡም፣ በዲያቆን ድርሻዬና (ይኸን ስም ልብ ብላችሁ ያዙልኝ) በአንድ ሌላ መሪጌታ ተጽፎ ቀረበላቸው። ውሳኔውም፣ ፩ኛ ድብራችን ውስጥ የታጋይ ጳውሎስ ስም እንዳይጠራ፣ ፪ኛ ማንኛውም ካህን ቅድስት ማርያም ውስጥ በመደበኛነት እያገለገለ፣ ወደሥላሴም ሂዶ ቢያገለግል፣ ከማርያም ቤተክርስቲያን ግልጋሎቱ እንደሚግለል በሙሉ ድምጽ ወስነው ተማምነው ተፈራርሙ። መዘምራንም እንደዚሁ። የዲያቆን ድርሻዬ ፊርማም እስከ ዛሬ ከዚያ ሳይደበዝዝ ከውሳኔ ወረቀቱ አፍጥጦ ያየናል። ውሳኔአቸውንም ለሰበካ ጉባኤው አመራር በጽሑፍ አስታወቁ። አመራሩም ለጠቅላላ የሰበካ ጉባዔ አቀረበ። ጥቅላላ ጉባዔውም በጭብጨባና በዕልልታ ውሳኔአቸውን በአንድ ትንፋሽ አጸደቀ። የቤተክርስትያኑ አባላትም ሆኑ ካህናት ግን ከፈለጉ፣ እዚያም ሄደው አያገለግሉ እንጂ፣ ቅዳሴ ቢሳትፉ ችግር እንደማይኖረው ተወሰነ። ይኸን ውሳኔ እንዲወሰንም ሰውን ሁሉ ካሳመኑት ዋነኛውና ግምባር ቀደሙ ተዋናይ፣ በጉብዝናው የተደነቀ ዲያቆን ድርሻዬ ነበር። አይ ዲያቆን ድርሻዬ! የዛሬን አያርገውና ያኔ ወኔው ነበረቻ! በዚህ ውሳኔ፣ ቤተክርስቲያኗ የአባ ጳውሎስን ስም ጠርታ አትጸልይ እንጂ፣ ከእናት ቤተክርስቲያኗ ያልተገነጠለች፣ አሁንም በአዲስ አበባው ሲኖዶስ ሥር ናት።

# ውሻ በቀደደ ጅብ ይገባል።

በአሁኑ ሰዓት፣ የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁንና፣ የቤተ ክርስትያናችንን ግዥ ዕዳ ከፍለን ወደ መጨረሱ ተቃርበናል። ከ£1 700 000 £1 00 000ውን ከፍለን £100 000 ብቻ ይቀርብናል። በዚህ ምክንያት የወያኔ ዓይን ደም ለብሷል። ቂመኛው ፓትርያርክ ታዲያ የምናደርገውን ሁሉ በጆሮ ጠቢዎቻቸው በኰል ይከታተሉታናል። ውስጥ የነበሩት አሽክሮቻቸው ተጠራርገው ስለወጡብቸው፣ ምንም ዓይነት ችግር መፍጠር አለመቻላቸው አብግኖአቸዋል። በዚህ ምክንያት፣ ከለንደን አገር ቤት የመልለሱትን ኢትዮጵያውን ሥራዬ ብለው ተለሳልሰው ማጥመድ ያዙ። ምሳ ማብላት፣ ሽልማት መስጠት አበዙ። ፍቅር በፍቅር! "የጅብ ፍቅር እስኪቸግር" እንዲሉ!

ያንን ቆራጥ ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ ታጥቀው ከተነሱት አንዱ ዲያቆን ድርሻዬ መሆኑን ገልጬአለሁ። ዳሩ ምን ያደርጋል። ዲያቆን ድርሻዬ ከጊዜ በኋላ እየተንሸራተተብን መጣ። በመጀመሪያ ደረጃ፣ የድብሩን አስተዳዳሪ መላከጽዮን ቆሞስ አባ ግርማን ጥምድ አድርጎ ያዛቸው። ለነገሩ የደብር አስተዳዳሪዎችን የመጥላት አባዜ አለበት መሰለኝ። ቀሲስ ብርሀኑ ላይም ተመሳሳይ በደል አድርሶባቸው ነበር። የኢትዮጵያን ሚሌኒየም ለንደን ላይ ቤተክርስትያኗን ይዘን ማዘጋጀት ስንጀምር አንድ ቁጥር ተቃዋሚ ሆኖ የቀረበን ማንም ሳይሆን፣ የኛው ያልነው፣ ዲያቆን ድርሻዬ ነበር። "ምን ነካው አልን?"፣ ስፍስፍ ብለን የምንወደው ሰዎች። እንዲያም ሆኖ ታዲያ እኛ ተሳክቶሎን በዓለም ተደርጎ በማያውቅ መጠን ሚሌኒየሙን በዓል ደግሰን ትራፋልጋር አደባባይ (Trafalgar Square) ላይ በመጀመሪያ ቤተክርስቲያናችንን አስቀደምን፣ በመዝሙር፣ በዜማ ዕምነታችንና ታሪካችንን አስተዋውቀን ካበቃን በኋላ አላፊ አግዳሚውን በአገራችን ባሕላዊ ዘፈንና ውዝዋዜ ልቡን አቀለጥነው። ዲያቆን ድርሻዬም ያን ማታ ሕዝቡ መሀል ገብቶ ላቡ ጠብ እስክትል ሲጨፍር አይቼው በጣም ደስ ብሎኝ፣ እጄን ዘርግቼ እንኳን አደረሰህ ብዬ ጨብጬዋለሁ።

ከዚህ በኋላ፣ ዲያቆን ድርሻዬ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ፣ ለዘጠኝ ወራት አካባቢ ተቀምጦ ተመልሷል። እሱ መንግስታዊ ባለሆነ በጎ አድራጎት ድርጅት (NGO) ውስጥ ሠራሁ ቢለንም፣ እኛ አንድ የግል ባንክ ውስጥ ሲሠራ እንደነበረ መረጃ አግኝተናል። ዋናው ቁም-ነገር ያ አይደለም። እንዲያው ወንደማችን አዲስ አበባ ያን ያህል ጊዜ ሲቀመጥ ታጋይ ጳውሎስ የሚያስቀድሱበት አካባቢ ሂዶ በመተታቸው ተለክፎ ይሆን? ከሄደ መቸም አንድ ነገር ሳያስነኩት አይልቁትም። ወፍጮ ቤት የገባ ዱቄት እንዲሉ።

ዲያቆን ድርሻዬ አዲስ አበባ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ትልቁ ሥራው አድርጎ የያዘው፣ እሱ አርሱ አርቅቆ ያወጣውን ድንብ ጥሶ፣ ወደ ሥላሴ የጎረፉትን የአባ ጳውሎስን ሰዎች ወደ ርዕሰ አድባራት ደብረጽዮን ቅደስተ ማርያም መመለስ ሆነ። ሀሳቡን ወደ ካህናት ጉባኤ አቅርቦ አልተቀበሉለትም። እሱ እራሱ ያሰረውን ቋጠሮ ለመፍታት ውሉ ጠፋበት። ሁሉንም እንደገና ለመቀልበስ የሚይዒጥጠው ቋጥኝ የለም። ይኽን አስገራሚ አጀንዳ አንስተው ካህናት የተንጋገሩበትንና ኃይል ቃል የተለዋወጡበት ጉዳይ፣ በሚያስገርም ሁኔታ ተቀርጾ በዩ-ትዩብ (youtube) ተለቀቀ። ማን ቀረጸው? ይኸ የወያኔ ሥራ እንጂ የምንም ድኅነኛ ሰው ሥራ አይደለም። ይኸ ሌብነት ነው። ምን ዓይነት ስውር ካሜራ ነው የተጠቀሙት? ጥቅሙስ ምንድነው? ምስጢርስ ማባከን ለማን ይበጃል? የታወቀ ነገር ያለም። በነገራችን ላይ በአዲስ አባባ ተቃዋሚዎች በራቸውን ዘግተው የተወያዩትን፣ ወያኔ በነጋታው በራሱ ጋዜጦች ያወጣ እንደ ነበረ የቅርብ ቀን ትዝታችን ነው።

ዲያቆን ድርሻዬ ደብዳቤ ጽፎ እያዞረ የተወሰኑ ካህናትን አስፈርመ (አባሪ አንድ ይመልከቱ)። እስካሁን ደብዳቤው ቃለ ጉባዔ ይሁን ወይም ስሞታ (petition) የታወቀ ነገር የለም። የደብሩ አስተዳዳሪ ቦታ በግልጽ አልተፈረመም። በእጅ ዲቆዮን ድርሻዬ በሰጠን ቅጅ ላይ የሊቀ ዲያቆን ተረፈ ቦታ በግልጽ አልተፈረመም። ዳሩ ግን በአንድ በቫይረስ በተበከለ ነጻ ድረ-ገጽ ላይ በወጣው ቅጂ ላይ ቦታው "ፊቃድ" የሚል ተጽፏበታል፣ ተራ ቁጥሩንም ለቋል። ድያቆን አባተ ቦታ፣ ከላይና ከታች "ሌሎች" ሲፈርሙ፣ ቦታውን ስለሞሉት የፈረመ አስመስለውታል። የመሪጌታ ዓለማየሁ ቦታ "ፊቃድ" የሚል ተጽፎበታል። ሌሎችም መፈረማቸው በጣም አጠራጣሪ ነው። እንዲያውም ከሚገርመው፣ ወንጌልን ልቅም አድርገው የሚያውቁ፣ በየበዓሉና በየሰንበቱ፣ የሚቀድሱና የሚያስተምሩ፣ የካህናት ጉባዔ አባላት፣ እንደ ቀሲስ ዳዊት አበበ፣ መሪጌታ አዲስ፣ መሪጌታ ሄኖክ፣ ዲይቆን እስራኤል እና ዲያቆን ዘርይሁን የመሳሰሉትን፣ በዚህ የካህናት ጉባዔ ነው ከተባለ ጉደኛ ቃለ መዝገብ ላይ፣ ለምን አልተካተቱም? ይኽች ነገር የዲያቆን ድርሻዬ የገዛ ራሱ ድርሰት ናት።

ይኸ ደብዳቤና ስሞታ፣ በደፈናው የሚለው ከየትም ደብር ይምጡ ከየት፣ ከአሜሪካ ሲኖዶስም ይሁን ከኢትዮጵያ፣ የቤተክርስቲያን አባቶች ወደ ርዕሰ አድባራስት ደብረጽዮን ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሲመጡ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያገለግሉ ይፈቀድላቸው፣ የኛም ካህናት ሌላ ቦታ ሂደው በነጻነት ይቀድሱ።" የሚል፣ የፊተኛውን ውሳኔ የሚሽር ነው። አሀ! ይኽማ በደፈናው እንዴት ይሆናል? በበር የወጡትን በመስኮት ልናስገባ? አይሆንም። በሩ ብቻ ሳይሆን በታጋይ ጳውሎስ ልጆች ላይ መስኮቱም ሳይቀር ገጥም ተደርጎ ይቀርቀር!!!

በሌላ አነጋገር፣ ክዚህ ቤተክርስቲያን እራሳቸውን ያገለሉ የታጋይ ጳውሎስ ሰዎች እንደገና እዚህ ቅዱስ ስፍራ እንዲመለሱ ዕድል ይሰጣቸው ነው ድርሻየዬ የሚለን። ሞኝህን ፈልግ ወዳጄ! ግራም ነፈሰ ቀኝ፣ ከፍ አለ ዝቅ፣ ቀመም ተቀመጠ፣ ተዘረጋውም ታጠፈ፣ ያለምንም ወለም-ዘለም የዲያቆን ድርሻዬ ጽሑፍ የሚለው ይኽቹኑ ነውና፣ ሌላ ሌላ ነገሩን ይተወው። ሌላው ክስ እንቶ ፈንቶ ገብስ ነው። እስቲ የዲያቆን ድርሻዬን ጥያቄ እንቀበል እንበል። ምናለበት፣ መጥተው ይቀድሱ፤ ቤተክርስቲያን ቤተክርስቲያን ነው፣ ምን አለ ብንል፣ የታጋይ ጳውሎስን ስም ሊጠሩብን አይደል? ከተፈቀደላቸው "አይምጡብን" የተባሉት አባ እንጦስ፣ የታጋይ ጳውሎስ ልዑክ ስላሴ አሉ፣ ሹልክ ብለው ሊገቡብን አይደል? እኚህ አባት ከአሁን ቀደም ሶስት ገጽ ደብዳቤ ጽፈው፣ "እመጣለሁ፣ የአባ ጳውሎስ ስም እንዳልጠራ የሚከለክለኝ ማነው? እስቲ ወንዱ ይምጣ አያዋለሁ!" ብለው የዛቱትን የድፍረትና የንቀት ዛቻ፣ ዲያቆን ድርሻዬ ልቅም አድርጓት ያውቃታል። መቅደስ ውስጥ ገብተው አባ

ጳውሎስ እያሉ ጸሎት ቢጀምሩ፣ ዓላማቸውን በግልጽ እያወቅን ለነገር ትንኮሻ ዕድል መስጠታች አይደል? አንዴ መቅደሱ ላይ ከሆኑ፣ "አባ ጳውሎስ" እንዳይሉ ዕውነትም ማን አባቱ ይከለክላቸዋል - ልክ እራሳቸው እንደዛቱት። የአባ ጳውሎስን ስም ጠርተው አይጸልዩ ተብለው ቢነገሩ "ዞር በል" ሊሉ አይደለ? አንድ ሁለት እየተባለ ጽብ ሊነሳ ነው። ከውስጥ በካህናት መሀል ጠብ ባይነሳ፣ አንጀቱ የቆሰለ ምዕምን ግብግብ ሊፈጥር ነው። ከዚያስ? መከረኛ ፖሊስ ሊመጣና ጣጣ ውስጥ ልንገባ። ቤተክርሲያኒቱም የጥል አውድማ ልትሆን አይደል?

እንግዲህ ከዚህ ባሻገር፣ ዲያቆን ድርሻዬ ስም እያጠፋ፣ ፊርማ እያስፈረመ፣ ምዕምናን ለማሳደም ሌት ተቀን የሚለውፋው፣ የአሁኑ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ቆሙስ አባ ግርማ ወይ እንደ አቡነ ዮሐንስ ብግን ብለው ቆሽታቸው ድብኖ እንዲሞቱ፣ ካልሆነም ልክ እንደቀሲስ ብርሀኑ አገር ጥለው እንዲሸሹና ደቂቀ ጳውሎስን መርቶ መልሶ ሊያስገባቸው መሆን አለበት። ምን አለ፣ አሁንማ ቤተክርስቲያኗ ተገዝታለች! የተጋይ ጳውሎስ ደንገጡሮች መጥተው ይረከቧት እንጂ! በየአገሩ ያሉት የኢትዮጵያ ኤምባሲ ሕንጻዎች ወያኔዎች፣ እንደመሬታችን ሊቸበችቡ ሲሯሯጡ እንዳየነው ሁሉ፣ ታጋይ ጳውሎስም ይኽችኑ መከራ አይተን የገዛናትን ሕንጻ ተርክበው እንደገና ስደተኛውን ያለቤትክርስቲያን ሊያስቀርን አቅደው መሆን አለበት እነ ዲያቆን ድርሻዬን የመለመሉት። ይኽች የታጋይ ጳውሎስ ታክቲክና የማይሰምር የዲያቆን ድርሻዬ ተልዕኮ መሆኗ ደርሰንባታል። ጎመን በጤና! እነሱም እዚያው በሰላም ይቀመጡ እኛም በሰላም እዚህችው እንኑር። ግን አንድ ነገር ላስምርበት። እንዲያው ምንም ይሁን ምን፣ ታጋይ ጳውሎስ ልክ እንደዲያብሎስ ሊያምሱን፣ ሊበጠብጡን ዕድል ሊኖራቸው ይችል ይሆናል እንጂ፣ ርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረጽዮንን እንኳን በእጃቸው ሊያስገቧት ይቅርና፣ ንክችም ለማድረግ ዕድል እንደማይኖራቸው አውቀው ተስፋቸውን ቆርጠው ይረፉ። ከታዘዘልን ጠባቂ መልአኩ በስተጀርባ፣ እያንዳንዳችን ምዕምናን ለእናት የስደት ቤተክርስቲያናችን ነጻነት ዘብ እንቆማለን። ስለዚህ እያወቅን ደቂቀ ጳውሎስን ወደ ቤተክርስቲያናችን አናስገባቸውም።

ይኸ ነገር አንድ የሰማሁትን ታሪክ አስታወሰኝ። መላከ ጽዮን ቆሙስ አባ ግርማ ከበደ ከዚህ ከለንደን ወደ እየሩሳሌም ይኸዳሉ። የእስራኤል አባቶቻችን ከሌላ አገር አንድ ሰው መጣ ሲባል እንኳን ለካህንና ለተራውም ክርስቲያን እንዴት እንደሚንገበገቡና እንደሚንከባከቡ እኔ ምስክር ነኝ። ታዲያ እኚህ አባት "ተውኝ" እያሉ እምቢ ተብለው "ካልቀደሱ" ይባሉና ተጎትተው መቅደስ ይገባሉ። ሥርዓቱን አካሄዱን በደንብ ተከትለው ሂደው የታጋይ ጳውሎስ ስም መጠራት ያለበት ቦት ሲደርሱ ዘለልውት "ለብጹዕ ወቅዱል ሊቀ ጳጳስ አባ ማቲያስ፣ ለሊቃነ ጳጳሳት፣ ጳጳሳት፣ ዔጵስ ቆጶሳት፣ ለካህናት፣ ለዲያቆናት፣ ለምዕምናን" ጸልየው እርፍ። እዚያ የነበሩ መንኮሳትና ቀሳውስት ክው ብለው ቀሩ። "ምነው አባ" ብሏቸው፣ "ውይ! ውይ! ውይ! ይቅርታ! ያለሁበትን ጨርሶ ረስቼው ነው። ለንደን ሳገለግል ስማቸውን ስለማናነሳ ለምዶብኝ ምኑንም ሳላስብ፣ እዚህም ደገምኩት። ለንዶን ያለሁ መስሎኝ ስርዓቱን ብቻ ላለመሳሳት ጥንቃቄ ላይ ማትኰሬ ነበር።" አሉና አረፉት። መቸም እሱ የማያውቀው የለም ብለው ነው መሰል በዚህ ሁኔታ እንዳለፉ ኢየሩሳለም እየሳቀ ያወሳላቸዋል። ኢየሩሳሌምስ ሳያውቁ ነው ጉድ የሆኑት፣ እኛ እያወቅን በተገላቢጦሹ እዚህ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ቢደገም ምን ሊባል ነው?

ዲያቆን ድርሻዬ ከልቡ ይሁን የታጋይ ጳውሎስን መልዕክት ተሸክሞ አይታወቅ፣ ይኸን ነገር ይዞ ሲያናፍስ፣ ቃለ ጉባኤ ነው ያለውን እያባዛ ሲበትን፣ ሕዝቡን ስልችት አድርጎት፣ የቤትክርሲያኗን አስተዳደር፣ "ምነው ይኸን ሰውዬ ዝም ብታስኙልን፣" ብለን ወተወትን። እነሱም በመስማማት ልናቆመው እየሞክርን ነው አሉን። መጨረሻ ላይ ስድቡ ሲበዛባቸው ነው መሰል፣ ማስጠንቀቂይ ጻፉለት። ከዚያማ ባሰበት። የተለያዩ ስድቦችን ጨምሮ፣ ገንዘብ ተመዘበረ ብሎ፣ ቀኖና ፈረሰ ብሎ፣ ጨምሮ ጨማምሮ፣ ኢትዮሚዲያ (Ethiomedia) ድህረ ግጽ ላይ ለአንድ ቀንም ብትሆን ማውጣት ቻለ። ጉድ ነው። ኢትዮሚዲያ እስካሁን የታወቀው ወያኔና ሊቀ መኳሱ ታጋይ ጳውሎስ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፍጽሙትን ደባ በማጋለጥ ነበር። እኛም እዚያ ላይ ነበር የወያኔና የታጋይ ጳውሎስን ጉድ የምንዘከዝከው። ታዲያ "በገዛ ጥይቱ ይቆስላል ብልቱ" ሆነብንና በኛው በወያኔ ተቃዋሚዎች ድህረ ግጽ የአባ ጳውሎስን ሰዎች ስሞታ እና የንጹሐንን ስም ማጉደፊያ ገበታ አድርጎ

ሊጠቀምበት ሞክረ። እግዚአብሔር ይስጣቸው፣ የድህረ ገጹ አዘጋጆች የስሞታውን ውስጠ ምስጢር ሲረዱት አዝነው፣ ይቅርታ ጠይቀው አወረዱት። እኛም አንድ ጥፋት አጠፋን። ሌሎቹን አገር ወዳድ የወያኔ ተቃዋሚ ድህረ ገጾችን ማስጠንቀቅ ነበረብን። አላደረግነውም። ያቺን የኛን ድክመት ተጠቅሞ አሁንም ዲይቆን ድርሻዬ አጨበርብሮ ሌላው ታዋቂ እና የነጻ መረጃ ምንጭ በሆነው በኢ. ኤም ኤፍ (EMF) ላይ ለማውጣት ቻለ። እንደገና እነሱም የዚያን ስሞታ ውስጠ ምስጢር ሲረዱ፣ አዘጋጆቹ የታጋይ ጳውሎስ ሰዎች ሰይጣናዊ መልዕክት መሆኑን ተረድተው አነሱት። ከዚያ በኋላ ዲያቆን ድርሻዬ በተለያየ ስም "ለምን አነሳችሁ" ብሎ በኢ-ሜል "እሪ" አለባቸው። "ወያኔዎች አሞኙአችሁ" እስከማለትም ደረሰ።

እኔ የገረመኝ፣ እንዲህ ዓይነት የስም ማጥፋት ነገር ማውጣት የሚወዱት የወያኔ ድህረ ገጾች አሉለት። በዓላማቸውም አንድ ናቸው። ለምን ወደዚያ አልላከም? ዓይጋ የሚባል ድህረ ገጽ ይኸን ቢያገኝማ በደስታ ነበር የሚለጥፍለት። ወደ አገር ቤት ተመልሶ ሲሄድም፣ ለውለታው ጥሩ ወፍራም ደሞዝ ያለው "የመንግሥት" ሥራና ስልጣን ይጠብቀው ነበር። እንዲያውም፣ በታጋይ ጳውሎስ ሳምባ በሚተነፍሰው፣ ለነጉሴ ወልድማርያም ሬዲዮ ዓይጋ ያስተላልፍለት ነበር። ንጉሴ ወልድማርያም የወያኔ ሆድ አደር ጋዜጠኛ ነው። አላ ሙዲ፣ የሚለፍፍበት ሬዲዮ ግዝቶ ሰጥቶታል። ታጋይ ጳውሎስ $100 000 የአሜሪካን ዶላር ከቤተክርስቲያኗ መዝብረው በበለጠ የወያኔን ጡሩንባ እንዲነፋ ሰጡት ተብሎ በሲኖዶሱ አባቶች ባለፈው ጊዜ የተወነጀሉበት ጉዳይ ነው። የዲያቆን ድርሻዬ የአዞ እምባ፣ ሬድዮ ላይም የመውጣትና የወያኔያዊ ተልዕኮውን በሰላም መወጣት በቻለ ነበር። ከእዚህ ከኛ ከተቃዋሚዎች ጋር ምን አንከራተተው? ይኸን ሬዲዮ በተመለከተ ደጀሰላም የተባለ ድረ ገጽ ሲኖዶሱን ጠቅሶ እንዲህ ይላል፡

> *"ፓትርያርኩ ቤተክርስቲያን አባቶች መካከል (ከቀድሞው ፓትርያርክና ከሌሎች አባቶች ጋር ያለውን) ልዩነት ከማጥበብ ይልቅ እያሰፉ ቤተክርስቲያን እንድትከፈል የሚያደርጉት ጥረት ሳያንስ በሀገር ቤት አስተዳደርም ዘመዶቻቸውን በመሾም ሀብቷ እንዲባክን ማድረጋቸው በተጠቀሰበት በዚህ ጉባዔ ዝናውን በውጪ ሀገርም ለማስነገር አሜሪካ ለሚገኘው የሀገር ፍቅር ሬዲዮ አስር ሺህ ዶላር መስጠታቸው ተገልጿል። አቶ ንጉሴ ወ/ማርያም ለተባለ ዲሲና አካባቢው ጋዜጠኛ 100 ሺህ ብር (ዶላር) ሰጥተዋል የተባሉት ፓትርያርክ ጳውሎስ በርግጥም ይህንን አድርገው ከሆነ በቤተ ክርስቲያኒቱ ታሪክ ገዳሞችና አድባራት እንዲሁም ሊቃውንት በችጋር እየተሰደዱ ሳሉ ገንዘቡን ያለ ርህራሄ ያባከኑ መሪ ያሰኛቸዋል።"* http://www.dejeselam.org/2009/05/blog-post_27.html

ለንጉሴ ወልደማርያምማያም ሲያንሰው ነው? አንድ ቁጥር አፈቀላጤአቸው አይደል! ለማንኛውም ንጉሤና ታግይ ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገናኙ የሆኑትን ለማየት የሚፈልግ፣ የሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ፊልማቸውን ማየት ይችላል።

http://www.youtube.com/watch?v=n0AR_zscVFs&search=endale%20getahun%20abune%20paulos

ለማንኛውም ለድርሻዬ የት ቢሄድ እንደሚመቸው ለመጠቁም እንጂ ከኛ ጉዳይ ጋር አይያያዝም። ለማንኛውም ድርሻዬ፣ የታጋይ ጳውሎስን ሰዎች መልሶ የማምጣቱ ነገር ቀላል አለመሆኑን ሲረዳ፣ "ዶሮ ባትበላም ጭሬ ታፈሳለች" ሆነበትና ሁለት ተጨማሪ አሉባልታዎች ጨምሮ ተነሳ። አንዱ አሉባልታ "ገንዘብ ተመዘበረ" የሚል ነው። እረ ይኸ ወንድማችን ደህናም ብቅል አስጠማ እንበል? እኛ ቤቱ ሲያፈስብን ማደሻ፣ የብድሩ ክፍያ ሲደርስ መክፈያ እያልን እንሯሯጣለን፣ የምን ገንዘብ ተርፎ ነው የሚመዘበረው? ገንዘብ ቢመዘበርማ በሀያ አምስት ዓመታት ውስጥ መግዛት ያልቻልነው ቤተክርስቲያን በአምስት ዓመታት ውስጥ ከ£1.5 ሚሊያን ብር በላይ ሰብስበን ሕንጻውን መግዛት ባልቻልን ነበር። ለመሆኑ ይኸ ወንድም፣ እናት ቤቱ ክርሲያናችን የነጠሩ ቻርተርድ አካውናታንቶችና የአካውንቲንግ ወይም የሂሳብ መዝገባ እያያዝ ምሑራን ልጆች በገፍ እንዳሏት

ያውቅ ይሆን፣ ዲያቆን ነው እንጂ እኮ በሂሳብ ሥራ ሊቅ አለመሆኑን ማን በነገረው! ገንዘቡ ለመመዝበሩ፣ ከአሉባልታ ባሻገር ምን መረጃ አለው? ይኽ ነገር ስም ማጥፋት በመሆኑ ፍርድ ቤት ሊያስጎትተው እንደሚችል ማንም አልመከረውም ልበል? ለማንኛውም ሁሉንም አውቃለሁ የሚል የማንን ምክር ይሰማል?

ስለገንዘብ መዘረፍ ካነሳን፣ አንድ ነገር መባል አለበት። አንድ እሑድ፣ ሙዳየ መጽዋዕት ይሰበሰብና በድንብ ተቆጥሮ፣ ቆጣሪዎቹ ተፈራርመው ቪካሬጅ ውስጥ ወዳለው ቢሮ ይወሰዳል። ፈቃደኛ የቤተክርሲቲያን የጽዳት ሠራተኛ እየተዘዋወረች ስታጸዳ ቆይታ የቪቻሪጁ በር ላይ ቁጭ ብላ ነበር። የሰንበት ትምህርት ቤት አባላትና የሰበካ ጉባኤው አመራር አባላት አጭር ስብሰባ ለማድረግ፣ የሚቀጥለው ክፍል ይሰበሰባሉ። ስብሰባውን ጨርሰው ወደቢሮ ሲመለልሱ በዕለቱ የተሰበሰበው ገንዘብና የአንድ የሰበካ ጉባዔ አመራር አባል ተንቀሳቃሽ ማስሊያ (laptop computer) ካስቀመጡበት ቦታ ያጡታል። ተደናግጠው ልግቷን "ዕቃ ጠፋ፣ የወሰደ ሰው አይተሻል?" ብለው ይጠይቁአታል። እሷም "እዚሁ ወጣ ገባ ከሚሉት ሰዎች አንደኛው ገብተው በሞባየላቸው እየተነጋገሩ፣ የጓሮውን በር ከፍተው ለጓደኛቸው አስረክበው ተመልሰው በፊት በር ሲወጡ አይቼአለሁ" አለች። "ምን ነው ዝም አልሽ አንቺ?" ቢሏት፣ "አይ እኔ ከመሀላችሁ ማናችሁ ኃላፊ እንደሆናችሁ፣ ማናኛችሁ እንዳልሆናችሁ ስለማላውቅ ስርቆት ይሆናል ብዬ አልጠረጥርኩም። ደሞ በዚህ ላይ፣ ምን የቀረጠው ክርስቲያን ነው የማርያምን ገንዘብ ደፍሮ የሚነካት ብዬ ልገምት?" አለች። ፖሊስ መጥቶ ሌባው ምን እንደሚመስል ስታብራራ፣ ከገለጻዋ ማንነቱ ማወቅ ተችሏል። በደፈናው የታጋይ ጳውሎስ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ገንዘብ ተመዘበረ እያሉ እዬዬአቸውን ሲያቀልጡ፣ የመርካቶ ሌባ ዘርፎ፣ ከሕዝቡ ጋር "ሌባ ሌባ" እያለ እየጮኸ የሚሮጠውን መንትፌ ያስታውሱናል። አሁን፣ የማርያምን ገንዝብ ዘርፎ ዕውን በጤና ሊቀመጥ ነው?።፣ የእምዬ ማርያምን ተአምር ጠብቁ።

ሌላው ክስ "ቀኖናው ፈረሰ ነው።" ወይ አንተ አምላክ! ጉድ ነው። እንዴ! ሊቃውንት እዚያችው ቁጭ ብለው፣ ለዚያውም እዚያው በእግራቸው ሥር ተቀምጦ የተማረ ዲያቆን ስለዚህ ጉዳይ አስተማሪዎቹ ፊት እንዲህ በድፍረት መናገር ይችላል? ያልወደድነውን ያህል ብዙዎቻችን በዚህ ወንድም አዘንናል።

ወንድማችን ምንም ሳይሆንለት ሲቀር የተወሰኑ ሰዎችን አሰባብስቦ አስፈርሞ (አንዳንዱ ስምና ፊርማ እራሱ ድርሻዬ ለመሆኑ ማረጋገጫ አለኝ - ኋላ ላይ አቀርበዋለሁ) አንድ የመጨረሻ ክስ ጽፎ ግልባጩን ለፖሊስ አስገባ። ከክሱ ጭብጦች መሀል እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

> ***As is clearly stipulated in our church's bylaw and special resolution, " Ethiopian Orthodox Tewahido Church St Mary of Debre Tsion will provide its services fairly and equally to its all members, regardless of their political opinion, ethnicity, region or locality", as the Church is the house of all believers from different political and cultural backgrounds. According to our special resolution, the Church will also not take side to any political party in any form and will not work alongside or give recognition to any Bishops /priests who do not follow the Church's rules and regulations, as well as participate in financial corruptions and affiliate with any political group. But, in contrary to the special resolution and bylaw, you prepared an illegal decree (regulation) in collaboration with your political groups, which will enable you: (a) to separate the Church from the mother Church's Holy Synod (i.e. to use the Church's funds and assets without accountability); (b) to isolate the Church from the other Ethiopian Orthodox Churches in the UK; and (c) to ban clergymen and regular members of our Church and trying to stop from going to other churches and in parallel, the other churches' clergymen not to come to our Church. This is also entirely divergent and contrary to the Canonical Law of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church, unless you are determined to run the Church as a private business centre only for few individuals, who have already financial vested interest and hatred/divisive political views. (ያሰመርኩብት እኔ ነኝ።)***

የታጋይ ጳውሎስ ተከታዮች በገዛ እጃቸው ገደል ሲገቡ አዩልኝ። በፈቃዳቸው ቤተክርስቲናችንን ለቀው ሂደውልን ከተገላገልናቸው በኋላ፣ አሁን ለመመለስ ሲሞክሩ መንገዱን ስለዘጋንባቸው፤ "በርዕሰ አድባራት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዘረኝነት በሰበካ ጉባኤውና በድብሩ አስተዳዳሩ በአባ ግርማ እየተካሄደ ነው" የሚል ክስ የመሠረቱቱ። በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ!! ይቅር ይበላቸው። ጉድ! ጉድ! ጉድ! ዘረኞችስ እንዳሉ የወያኔ ተከታዮች ናቸው። የኛ ቤተክርስቲያን የንጹህ ኢትዮጵያውያን መጠለያ ቤት ናት። አማራው፣ ጉራጌው፣ ኦሮሞው፣ ሀዲያው፣ ከምባታው፣ ጀማይካዊው፣ ኤርትራዊው፣ እንግለዛዊው (ዕውነቴን ነው የምላችሁ) ሁሉም ክርቲያን የሚርመሰመስባት ሀቀኛ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ናት። በየሳምንቱ ከእምዬ ማርያም ደጃፍ የማይጠፉ ብዙውን ጊዜ ትግርኛ የሚናገሩ እናቶች ምን ይበሉ? "ገንዘብ ዘረፉ"፣ "ቀኖና አፈረሱ"፤ ይግርማል። "ዘረኞች ሆኑ"፣ አ - ኦ! አያስኬድም። አቅጣጫ ቀይር! የዘረኝነት ጥንስስ ከነጋኑ፣ ከነዘር መንዘራዘሩ ያለው ወያኔ ቤት ነው። የእምዬን ወደ አብዬ!

# የየዋሁ ካህን ሥቃይ

በዚሁ ክስ በአምስተኛ ተራ ቁጥር ያስቀመጡት አሳፋሪ፣ የሚሰቀጥጥ ክስ አለ። የክሱ መሠረት እንዲህ ነው። አንድ ቄስ ገብረሀና (መስፍን) የሚባሉ፣ ድርሻዬ አባብሎ "የካህናት ቃለ ጉባኤ" ያለውን ያስፈረማቸዋል። ቤተክርስቲያኗን ብቻ በማገልገል የተጠመዱ "ምስኪን" የሚባሉ አባት ናቸው። ሰውንም ቀና ብለው አያዩም። አንድ ቀን አንድ ሰው እንዲህ ብሎ አጫወተኝ። የድርሻዬ ሰዎች እኚህን ቄስ ቤተክርስቲያን ገብተው እንዳይቀድሱ አስፈራርተዋቸዋል የሚል። የኔ ጥያቄ፣ "ለምን? ምን ሊጠቀም?" የሚል ነበር። "ዲያቆን ድርሻዬ፣ መላከ ጽዮን ቀሙስ አባ ግርማ፣ የሥላሴን ቀሳውስት እንዳይመለሱ እንቅፋት ስለሆኑበት፣ ካህናቱን እያሳደመ ነው። እኚህም "soft spot" (ለማሳመን የማይስቸግሩ) ስለሁኑ፣ እሳቸውን ለማግባባት ሞከረ። 'ሌሎቹ በሙሉ ተባብረውኛል። እርስዎ መቀደስ ካቆሙ፣ ሌሎቹም ለማቆም ተስማምተዋል። አባ ግርማ ብቻቸውን ይቀራሉ። ያኔ ቅዳሴ ይተጓጎላል። ቅዳሴ ሲቶጓጎል ሕዝቡ ጥያቄ ያቀርባል። የኛም ጥያቄ ያኔ ይመለሳል' ብሎ ሊያሳምናቸው ሞክረ" ተባልኩ። "አይ! ይኽ አሉባልታ ነው። ድርሻዬ የጌታን ቤተክርስቲያን ቅዳሴ እንዲተጓጎል ያን ያኽል ሂዶ ሽር አይሠራም" ብዬ ተከራከርኩ። ግን እሳቸውስ ምን መለሱ ብዬ ለጠይቅኩት ጥያቄ፣ የተሰጠኝ መልስ፣ "ሰውዬው የእግዚአበሔርን ቤት ከማጠን፣ ከመቀደስ አቁም የሚለኝን ሰው አልተባበረውም።' አሉት" ተባልኩ። ከዚያም "ብታቆም አቁም፣ አለበለዚያ ዋጋህን ታገኛለህ" ተባሉ። እሳቸውም ነገሩን በዚያ አልተውም ተባለ። መላከ ጽዮን አባ ግርማ ጋ ሂደው የሆነውን ሁሉ ነገሩአቸው። ለነገሩ ከአስተዳዳሪው ጋር ያሉ፣ ብዙ ካህናትና ምዕምናን ስላሉ፣ ይኽን ያህል የሚይሳጋም አልነበረም። ምዕምኑ እንደሆነ እንደ ግድግዳ ተገጥግጠ፣ የታጋይ ጳውሎስን ደንግጡሮች እንደሚከላከል የታወቀ ነው። ከሕዝቡ በአሻገር ምንም መሥራት እንደማይቻል እነዚህ ጭብጥ የማይሞሉ በጥቅማ ጥቅም የተያዙ ሰዎች የማይረዱበት ምክንያት ጨርሶ አይገባኝም።

ይኽ ከሆነና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ አንድ በጣም የሚሰቀጥጥ ነገር ተፈጠረ። በእኚህ የዋህ ካህን ላይ አይናችን እያየ ተሰምቶ የማይታወቅ ግፍ ደረሰባቸው። ቄሱ ጥሎባቸው፣ የታመመ ሰው አለ ከተባለ፣ መሮጥና፣ ለዚያ ሰው መጸለይ እንደ ግዴታቸው ወስደውታል። ኑ ቤቴን ጸብል እርጩ ከተባሉ አገር አቋርጠው መሄድ ነው። እሳቸው ስደተኛውን ኢትዮጵያዊ በሙሉ የሚያዩት ልክ እትዮጵያ እንዳሉት የክርስትና ልጆቻቸው ነው። ታዲያ እንደተረዳሁት ከሆነ አንዲት በዕድሜአቸው ገፋ ያሉ ወይዘሮ እኝህን በፈውስ ጸሎት ዝናቸው የገነነውን አባት ይቀርቡና እንደሚያማቸው ገልጸው እንዲጸልዩላቸው ይጠይቁአቸዋል። በዚህም ሰበብ፣ ቄሱ እቤታቸው ድረስ ይኸዱና፣ ጸልየውላቸው፣ ሜሮን ቀብተዋቸው፣ እንዴት መንፈሳዊ መሆን እንደሚቻል መክረው፣ ስለኢየሩሳሌም ጉዞም አንዳንድ ምክር ሰጥተዋቸው፣ በሰላም ምሳቸውን እዚያው በልተው፣ ለሚካኤል ቤትክርስቲያን የሚሰጥ

ገንዘብ £20 ተቀብለው፣ ለራሳቸውም ከምስጋና ጋር ታክሲ ተከፍሎላቸው፣ አገር ደኅና ነው ብለው ወደቤታቸው ይመለሳሉ። ከወር በኋላ፣ እሜቴ እየገሰገሱ ቤተክርስቲያን ይመጡና፣ ቀሙስ አባ ግርማን ጠርተው፤ "እኚህ አባት ያለፈቃዴ ልብሴን አስወልቀውኛል፣ ሰውነቴን ነካክተው ሜሮን ቀብተውኛል። ስለዚህ በዚህ ቤተክርስቲያን እንዳይቀድሱ ይታገዱልኝ" የሚል አቤቶታ ያቀርባሉ። ቀሳውስት ይደነግጣሉ። መላከ ጽዮን ቀሙስ አባ ግርማም የሚይዙትን የሚጨብጡትን ያጣሉ። እንዲህ ዓይነት ክስ ታይቶም፣ ተሰምቶም አይታወቅማ። "ቤት መጥተው ጸብል ይርጩልኝ" እየተባሉ ቀሶቻችን ስንት ገዜ በየበቶቻችን ተጎትተዋል። መንኰሴውም ያ መቸም ሰይጣን ያመጣብን ጣጣ ነውና ብለው ሴትዮዋን አረጋግተው፣ ቀጠሮ ሰጥተው፣ ቄሱን ይጠሩአቸዋል። ቄሱ አገር ድኅና ነው ብለው ለአገልግሎት የተጠሩ መስሏቸው እየሮጡ ሲደርሱ፣ ነገር ዓለሙ ድብልቅልቁ ወጥቶ ተገለባብጠ ይጠብቃቸዋል። የተከሰሱበትን ወንጅል ሲሰሙ፣ በጣም ይናደዱና፣ ታቦተ ጽዮን ፊት ተንበርክከው፣ "ፍረጂኝ" እያሉ መጨህ ይጀምራሉ። ቀሳውስቱ "ተው ተው ብለው" ከተንበረከኩበት ያነሱአቸውና ይቆጡአቸዋል። የደረሰች ልጃቸው የሚነጋገሩትን በድምጽ መቅረጫ ስትቀዳ፣ መላከ ጽይሆን ቀሙስ አባ ግርማ ይነቁባትና እጅ ከፍንጅ ይይዟታል። "ምን እያደረግሽ ነው?" ብለው ሲያፈጡባት፣ የምትለው ጠፍቷት፣ "ፖሊሶች ቅጂ ብለውኝ ነው" ብላ እዚያ በተሰበሰቡት በለቀጠበብት ዓለማየሁ ፊት ተናገረች። ነገሩ እንዳይክር መልአከ ጽዩን አበረዱት እንጂ፣ በዚህ ብቻ ልጅቷ እስር ቤት የምተወረወርበት ጉዳይ ነበር። የፖሊስን ስም በወንጀል መጠቀም አይቻልም። መላከ ጽዮን፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የዕርቅ መሆን አለበት ብለው ሁሉንም አሳለፉት። ይቅርታ እንዲጠያየቁ ሲጠየቁ፣ ቄሱ በጣም በመናደድ፣ "ጌታ እየሱስ ያዘዘኝን መልካም ሥራ ስለሠራሁ ነው ይቅርታ የምጠይቀው?" በማለት በምሬት ሲናገሩ፣ እዚያ የነበሩት ካህን ተቆጥተዋቸው፣ ከሴትዮዋ ጋር ይቅርታ እንዲባባሉ ያደርጉአቸውል። ሁለቱም መስቀል ይዘው ይቅር ለመድኃኔዓለም ተባብለው አቡነ ዘብሰማያት ጸልየው ወደየቤታቸው ይኸዳሉ። ማን የተለየ ምክር እንደሰጣቸው እሳቸውና አንድ አምላካቸው ብቻ ያውቃል፣ ሴትዮዋ ምንም ሳይቆዩ ተንስተው ፖሊስ ጣቢያ ሂደው ክስ ይመሰርቱባቸዋል። እንደገና መሬት ተገለባበጠች። የዋሁ ቄስ እንደወንጀለኛ በፖሊስ ተይዘው ቀኑን ሙሉ ሲመረመሩ ውለው አደረው በሰላም ወደቤታቸው ተመለሱ። ይኸኔ ነበር፣ ድርሻዬና ተባባሪዎች ቄሱን ቀርበው፣ "ድሮም እኮ መክርንዎት ነበር። ከኛ ጋር ዝም ብለው ይተባበሩ። አባ ግርማ አያስጥሉዎትም። ከኛ ጋር ቢተባበሩ፣ ክሱን ውድቅ እናስደርግልዎታለን" ይሉአቸዋል። እሳቸውም፣ "ንጹሕ ከሆንኩ ክርስቶስና እመቤቴ ይታደጉኛል። ኃጢአተኛም ከሆንኩ፣ መጠጣት ያለብኝን ጽዋ እጠጣታለሁ። ሥጋዬን ለማዳን ብዬ፣ ከናንተ ጋር አልተባበርም።" በማለት አሳፍረው ላኩአቸው። አሁን ነገሩ በፍርድ ቤት ትይዟል። እንግዲህ እነ ድርሻዬ ካሉባልታ ገና ባሻገር ሕግ ስለማያቁ በፍርድ ቤት የተያዘው ጉዳይ፣ ሕግ ጥሰው በየውስጥ መሩቡ (internet) ሲበትኑት፣ እንደገና ለፖሊስ በገባውም ክስ ቀሙስ አባ ግርማን ይወነጅሉአቸዋል። የነታጋይ ጳውሎስ ቡድን ወንጀል፣ መቸ ተዘርዝሮ ያልቃል? አምላክ ብቻ ፍርዱን ይስጣቸው።

# "ትላልቆቹ ሰዎች"?

ዲያቆን ድርሻዬን ብዙዎቻችን ከዚህ በፊት እነወደው ስለነበረ፣ አብዛኞቻችንም በዕድሜ ታልቁም ስለሆንን፣ ምናልባት ምክራችንን ይሰማ እንደሆን ብለን ጥሩ፣ ጥሩ ሰዎችን መርጠን እንዲያናግሩት ላክንበት። ነገሩ እንዲህ ነው። ሌላ ተልዕኮ ይዞ ካልሆነ በስተቀር ይኸንን ብዙው ወዳጆቹ ጋር የሚያቀያይመውን አሉባልታ ቢተውና ወደ ክርቲያናዊ መንገድ እንዲመልስ አስጠየቅነው። ምክያቱንም ሲገልጹለት፣ ነገሩ "ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል" እንዲሉ፣ እናት ቤተክርስቲያኑን በዚህ አሉባልታና ክስ ሲያምሳትና ሲጎዳት ጠላቶቿ ዕድል አግኝተው ያጠቁአታል፣ ወጣት ምዕምናኖቿ ወደማይፈለግ ዕምነት ይሄዱሉ እና እንዲተው ለመኑት። ምን አለፋችሁ፣ ሰውዬው ዓላማ አለው። ምን እንዳላቸው ልንገራችሁ? "እኔ ምን ቸገረኝ። ነገሩን አቀጣጥዬዋሁ። ጉዳዩን ከትላልቅ ሰዎች ጋር አያይዤዋለሁ። እኔ እንደሆንኩ የማረገውን አውቀዋለሁ። ሰው ቢወደኝ፣ ሰው

ቢጠላኝ ደንታ የለኝም።” ነበር ብሎ በትዕቢት የመለሰላቸው። እነዚህ ትላልቅ ሰዎች ሰዎች እነማን ይሆኑ? እንግዲህ ፖሊስ ጽሕፈት ቤት በአስገባው የስሞታ ደብዳቤ ላይ የፈረሙ ጥቂት ሰዎች መሆን አሉባቸው። የስም ዝርዝራቸውና ፊርማቸው፣ ለፖሊስ ባገቡት ደብዳቤ ተዘርዝሮ፣ የኸውና እዚህ በአባሪ 2 ግርጌ ተቀምጦላችሁአል። ስለ ስሙ ዝርዝር ትንሽ ልበል፡፤ ከአንድ ካህንና አሥር ከማይበልጡ ግለሰቦች በስተቀር፣ ሌሎቹ የዲያቆን ድርሻዬ ፈጠራዎችና ፍጡሮች ናችው። ጊዜ አላጠፋም። ዝም ብላችሁ በቁ23 እና በ25 የተጻፉትን ስሞች ይመልከቱ። ሁለቱም Ms A. Asefa ናቸው። እጅ ጽሕፈቱም አንድ ነው።

በሺህ የሚቆጠሩት አባላት ያላት ቤተክርስቲያን፣ እንዲያው ጭብጥ የማይሞሉ የታጋይ ጳውሎስ ተከታዮች ዕውን ሊያሸንፉን ያስባሉ? “ብዙሀን ይመው” ማለት ምን ነብረ ትርጉሙ? ረሳሁት! ዳሩ ምን ያደርጋል፣ ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያን እንዳጋጣሚ ሁኖ ፊደል ከቆጠርን እራሳችንን ብቻ ነው የምንሰማው። የዲሞክራሲንም ሀ ሁ አናውቅም። ብዙሀን ይመው ሲባል ሰምተን ይሆናል! ትርጉሙን ማን ያስተምረን! ኢትዮጵያ ቢሆን እኮ እንዚህ ግንበ አስጠግተው ረሽነውን ነበር። ወይ ነዶ!

## መደምደሚያ

እናጠቃልል። “ተለምኖ ተለምኖ እምቢ ብሎ እንዲህ ያመረረው ወንድማችን እንዴሌሎቹ ሆድ አደሮች እንደ እነ ሰሎሞን ተካልኝ በሆዱ ተጠምዝዞ ወይስ ዲያብሎስ የሚባለው ሰይጣን ቁራጭ ተጠናውቶት?” የሚያሰኝ ደረጃ ላይ ደርሰናል። ወየነም አንልም። አልወየንምም አንልም። ብቻ ዲያቆን ድርሻዬ አንድ ነገር ግን ሁኗል እንበል። መላ ለመምታት እንዲያመቸን፣ እስቲ አንድ ወቅት ላይ የሆነውን ታሪክ እንመርምር።

ነገሩ እንዲህ ነው። ሁለት የቅድስት ማርያም ዲያቆናት፣ የድርሻዬ አብሮ አደግ ጓደኞች፣ ሊዳሩ ኢትዮጵያ ይሄዳሉ (እሱ መቸ ይሆን የሚዳረው?)። እንዲህ የሚል ዜና ደረሰን። “ድል” ያሉ ሠርጎች ተደግሰው ተበላ ተጠጣ። ተጨፈረ። ዲያቆን ድርሻዬም እዲስ አበባ ስልነበረ በዚያው አጋጣሚ ሠርገኛቸው ሆነ። ከዚያ በኋላ መልስ የሚባል ጋጋታ ተፈጠረ። ከቤት እቤት እየተጋበዙ መብላት መጠጣት ሆነ። አንድ የሁለቱም የወንድ ሙሽሮች ሌላ ጓደኛ ነበር። ይኸ ጓደኛቸው እንዳጋጣሚ ሁኖ የታጋይ ጳውሎስ የክርስትና ልጅ ነው አሉ። (ይቅርታ እዚህ ላይ - እኔ ቄሰ አንድ ልዩ የክርስትና ልጅ ሲኖረው ስሰማ የመጀመሪዬ ነው። ሁላችንም የክርስትና ልጆቻቸው ነበር የሚመስለኝ። አይ አለማወቄ!) ታዲያ ይኸ የታጋዩ ፓትርያርክ የክርስትና ልጅ ድግሶ ሁለቱን ጓደኞቹን መልስ መጥራት። አንድኛው ሙሽራ ሊቀ ዲያቆን ሳይመቸው ይቀርና ሌላው ሙሽራ፣ ሙሽሪቱን ሸጉጠ፣ ከለንደን ተግተልትለው ከሄዱት ጓደኞቹ ጋር መልሱ ቦታ ከቸች። እዚያ ሲደርሱ ሙሽሮቹ ሳይሆኑ የዕለቱ ኮከብ እንግዳ ማን ይመስላችሁአል? ከለንደን ሰው መጣ ሲባል ዕድሉ የማያመልጣቸው ታጋዩ ጵውሎስ ናቸዋ። ውስኪው እንደውሀ ፈሰሰ። ጮማው እንደ ዳቦ ተቦደሰ። ተበላ ተጠጣ። ተዘፈነ፡ ተጨፈረ። መጨረሻ ላይ የለንደኖቹ እንግዶች፣ ለበረከት (በረከት ስምዖን ማለቴ አይደለም) ተብሎ፣ ሠርገኞቹ አንድ በአንድ እንዲሰለፉና “ብፁዕነታቸው” (ኤጭ!) ፊት እንዲቀርቡ ተደረገ። አንድ ላይ ተሰልፈው ታጋዩ ፓትርያርክ ፊት ቀረቡ። ወይ ጉዴ! ሞኙ ካሜራ! መቼም የያዘውን አይለቅም፣ ጉድ ለመጣ ነው!

# ውይ! ውይ! ውይ የቁሉቢው!!! ይኸ ፎቶ የዲያቆን ድርሻዬ ነው ወይስ የዳማዊ ሙሉጌታ አሥራተ ካሳ?



በ

እዚህ ፎቶግራፍ ላይ እንደሚታዬው ከሆነ ታጋዩ ፓትርያርክ ልክ ከዚህ በፊት እንደሚያደርጉት፣ ከለንደን የመጡትን የክብር እንግዶች እያነጋገሩ፣ መስቀል ከነሐብሉ ሽለሙአቸው። ትክ ብላችሁ ተመልከቱ! እጃቸው አንዷን ሀብል ከነመስቀሉ እያነሳ ነው። ለመታሰቢያም እንደሞዴል ፎቶ ዘና ብለው ተነሱ። እንድሚታየው ከሆነ ድርሻዬ ጥርስ በጥርስ፣ ፍቀር በፍቅር ሁኗል። የፈገግታውን ሁኔታ እዩት፣ የእጁን አተጣጠፍ ተመልከቱት። ሌሎቹ ሰርገኞቹ ፊታቸው ተከልሎላቸዋል። እነዚህ ሰዎች ስጦታውንም ይቀበሉ፣ መስቀሉንም ይሳለሙ፤ (መላከ ጽዮን አባ ግርማ አንዴ ሲመክሩኝ "ማር በገባጣ አህያም ተጫነ፣ በደልጋሳ ፈርስ፣ ማርነቱን አይቀይርም" ብለውኛልና፣ እኔም ምናልባት ዕድሉ ቢያጋጥመኝ እሳለም ይሆናል - እንትፍ! እንትፍ! ጌታ ከዚያ ፈተና ይሰውረኝ)። ኢነዚያ ሠርገኞች ልዩ ተልዕኮም ከታጋይ ጳውሎስ ይዘው አልመጡም። አላሳደሙምም። ሊቀ ዲያቆን ድርሻዬ ታዲያ የታጋይ ጳውሎስን ተልዕኮ አንግቦ የተመለሰ ለመሆኑ ቅንጣት ታህል ጥርጣሬ የለንም። ምክንያቱ አንድ እግራቸው በኛ ቤተክርስቲያን ተክለው፣ ልባቸው የታጋይ ጳውሎስን ተልዕኮ አንግቦ የሚመላለሱ፣ ተይማራኪ የሆኑ ሰዎችን ለማሳደም ሌት ተቀን ያለመሰልቸት የሚማስነው ለነብሱ ወይስ ለሥጋው? ድርሻዬ በአንድ በኵል ለማያውቁት፣ "የአባ ጳውሎስ ተቃዋሚ ነኝ። አዲስ አበባ ስሄድ እንኳን መስቀላቸውን መሳለምን ፊታቸውም ስለሚያስጠላኝ አጠገባቸውም አልደረስኩም" እያለ ሲፎክር ተሰምቷል። ፎቶግራፉ የሚለን ግን ሌላ ነው።



እንግዲህ አንባቢ፣ እኔ ቀደም ብሎ ያልኩትን መልሼ ልበል። ታጋይ ጳውሎስ የሀይማኖት ሰው ሳይሆኑ የፖሊቲካና ይኽችን ዓለም አጣጥመው ገና ያልጨረሱ ሰው ናቸው። እንዲያውም የተቸገረ ሰው ለምልጃ ሲሄድባቸው፣ በቀጥታ መለስ ጋ እየደውሉ ጉዳይ ማስፈጽም የሚችሉ የወያኔ ሊቀ መኳስ ናቸው። ከሳቸው የሚተባበር፣ የሳቸውን ተልዕኮ ተቀብሎ የሚያምስን ሁሉ ወያኔ ነው። እኔ ሊቀ ዲያቆን ድርሻዬ ወየነ ማለቴ አይደለም። አልወየነምም ማለትም አልችልም። ዲያቆን ድርሻዬ ግን እራሱ ነድፎ፣ ጽፎ፣ አርቅቆ ያስጸደቀውን ሕገ ደንብ ለምን ለማፍረስ ፈለገ? መልሱን ከፎቶግራፉ ያገኙታል። ፎቶው አፍ አውጥቶ ይናገራላ!

ይኽ መልዕክት ለድርሻዬም ብቻ አይደለም። ድርሻዬ አንዴ ተዘፍቆበታል። "ጉዳዩን ትላልቅ ሰዎች ይዘውታል፣ እኔ እንደሆንኩ ተልዕኮየን ፈጽሜአለሁ፣" ለተባለላቸው፣ ሳያውቁም ሆነ እያወቁ "ማኖ" ለነኩት "ትላልቅ አዛውንቶች" ነው። ከድርሻዬ ጋር ተባብረው ለፖሊስ ባገባችሁት ጽሑፍ በፊርማችው ድርሻዬ አጋልጠአቸዋል። ማን ማን እንደሆናችሁ እናውቃለን። የምትሠሩትን አምናችሁበት ከሆነ፣ አንድ መውጫ እኮ አለ። ምናለ እኛን ከምታምሱን፣ አባ ጳውሎስ የሚመለኩበት ቤተክርስቲያን ሂዳቸው ከተመሳሳይ ወንድሞቻችሁና እህቶቻችሁ ጋር ተደባልቃችሁ በሰላም ለምንድነው በሰላም በፍቅር የማትኖሩት? አባ እንጦስ እንደሆኑ፣ "ትግርኛ ተናጋሪና ሌላው" ብለው እንደሚያመቻችሁ ሁለት ቤተክርስቲያናትን አዘጋጅተውላችኋል። ለምን እዚያው አትደባለቁም? የኛን እኮ በግድ ማፍረስ የለባችሁም። ከኛ መለየት ካልፈለጋችሁ፣ ግን ይኽን ክፉ ነገር የምታደርጉት አንድ ወይም የተወሰኑ ሰዎች ጠልታችሁ በቂም ተነሳስታችሁ ከሆነ፣ አምላካችን ቂመኛ አይወድምና ንስሐ ግቡ። ይልቅ ኑ አብረን ተቀምጠን ጽድቅን እንፈልግ። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተመካከርን ተወቃቅሰን ልዩነታችንን እንፈታ። ፍቅራችንን እናድስ። እያወቃችሁ ከሆነ ለታጋይ ጳውሎስ አሽከላ የተጠመዳችሁ፣ እኔ ትንሹ ወንዳማችሁ የምላው አለኝ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሳይሆን የምንኖረው የሕግ የበላይነት የተከበረባት አገር ነንና፣ አታሸንፉም። ስለዚህ በታጋይ ጳውሎስ የተዘረጋላችሁን ወጥመደና ተንኰል ተረድታችሁ፣ እራሳችሁን ከዚህ መሠሪይ ተግባር አርቁ። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ግለሰቦችን እንጉዳ ስትሉ እናት ቤቴክርስቲያንን ለቀን ጅቦች አሳልፋችሁ ለመስጠት የምትወጡትና የምትወርዱት እንኳን ሰውና እግዚአብሔርም አይወድላችሁም። ልዩነቶቻችንን በፍቅር እንፈታቸውለን። ውሻ በቀደደ ጅብ እንዳይገባ፣ ምክንያት አትሁኑ! ክርስትያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ናችሁና፣ ጌታ ከስሕተት ይሰውራችሁ። የእናታችን፣ የእመቤታችን ቅድስት ማርያም ቤትን በተመለከተ፣ ብዙም አንሰጋም። እንደ ከዚህ በፊቱ የታዘዙላት መላዕክት ከዚህ በፊት፣ ከታጋይ ጳውሎስ፣ ከሊቀ ካህናት ብርሁን ገብረአማኑኤል፣ ከአባ ሙሴ፣ ከአባ እንጦስ እንደጠብቁአት በክንፎቻቸው ክከእናንተ ፍላጻም ይሰውሩአታል። ታጋይ ጳውሎስ እንደሆኑ እንዲችው ቂማቸውን እንደቋጠሯት ወደሚጠሩበት ይወርዱአታል እንጂ፣ ርዕስ አድባራት ለንደን ደብረ ጽዮንን አያገኙአትም። አበቃ!

ስብሀት ለእዚአብሔር!

# አባሪዎች



25/11/2000 ዓ.ም

ለርዕሰ አድባራት ለንደን ደብረጽዮን ቅ/ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤተክርስቲያን ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት።

ለንደን።

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ጋር ይሁን፤ በማለት የአክብሮት ሰላምታችንን እናቀርባለን።

የደብራችን የካህናት ጉባዔ፡ ቤተክርስቲያናችን ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/አብያተክርስቲያናት ጋር ስለሚኖራት ግንኙነትና አባቶች ካህናትና ጳጳሳት በአካ ግድንትም ሆነ በግብዣ ወደ ቤተክርስቲያናችን ቢመጡ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን ሁኔታ አስመልክቶ በሰፊው ተወያይቶበታል።

ጉባኤው 3 አዘጋጅ አባላትን መርጦና ሰፋ ያለ ጊዜ ወስዶ በመወያየት የተስማማበትን ቃለ ጉባኤ ከዚህ የመሸኛ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆናችንን በአክብሮት እንገልጻለን።

ከመንፈሳዊ ሰላምታ ጋር።

ዲ/ድርባዬ ለማ።
የዕለቱ የካህናት ጉባኤው ቃለ ጉባኤ አዘጋጅ አባልና ጸሐፊ።

ግልባጭ ፤

ለሕግና ሥነሥርዓት ጉባኤ
ለቁጥጥር ኮሚቴ
ለሕንፃ ቤ/ክና ልማት ኮሚቴ
ለሰንበት ት/ቤት የአመራር ኮሚቴ

## አባሪ ሁለት

January 12, 2011

To: M.T. Abba Girma Kebede,
Priest in charge of Ethiopian Orthodox Tewahido Church St Mary of Debre Tsion
1 St Philip Square,
Queenstown Road,
Battersea,
London, SW8 3RT.

RE: Warning notice for your illegal and malicious action against prominent members of the Church who firmly oppose your: (a) discriminatory actions in the contrary to the Church's Equal Opportunities policy; (b) financial corruption and mismanagement of the Church's funds & assets; and (c) failure to carry out your duties & responsibilities in line of the Church's rules (Bylaws) and regulations.

As we all remember, four and half years back, you were elected to serve our church as priest in charge for three years. You also pledged oath in the name of the Lord at the General Assembly of the congregation to carry out your responsibilities in accordance with our Church's Parish rules (KALE AWADY & BYLAW) and Charity deeds. But, contrary to all these:

1. You have failed time and again, to work in line of our church's rules and regulations, particularly with regard to Equal Opportunities policy that could adequately provide equal and fair treatment for all members of the church by enabling them to serve or be served in the church in unity, peace and harmony. You have illegally extended your and the Parish council members/trustees' term of office for unconditionally (like African dictatorial leaders). Moreover, you've managed to dismantle, purposefully, the key institutions of the Church, such as the Clergy council, the Law & Order Council and Finance & Asset Inspection /Control committee that would challenge your illegal actions and make sure that all committees and staff /trustees are complying with the Church's rules, orders and regulations, particularly, in relation to the financial management of the Church's funds and assets/properties.

2. Instead of serving all clergymen and lay members of the Church in peace and harmony, you have purposely affiliated with few individuals who have divisive and hatred political views, and vested financial interest in the Church. In order to satisfy your group and use the Church's money and assets illegally, you have created division among the Ethiopian Orthodox Churches in the UK and discriminated the members who have different views from the group you have affiliated with. This is absolutely and utterly contradictory to our Christian belief, as well as the rule of law of the country (United Kingdom).

3. You have dismantled the internal finance/assets inspection/control committee and blocked independent investigations to the alleged financial corruptions/misconduct and the embezzlements of assets (diamonds, gold, silvers and other in-kind donations) allegedly committed by you and your groups from time to time (August 2004 – on-going). You have also made malicious and deceitful campaign against the clergymen and lay members who

are concerned with the alleged corruption and embezzlement of the Church's funds and assets and request independent investigation.

4. As is clearly stipulated in our church's bylaw and special resolution, " Ethiopian Orthodox Tewahido Church St Mary of Debre Tsion will provide its services fairly and equally to its all members, regardless of their political opinion, ethnicity, region or locality", as the Church is the house of all believers from different political and cultural backgrounds. According to our special resolution, the Church will also not take side to any political party in any form and will not work alongside or give recognition to any Bishops /priests who do not follow the Church's rules and regulations, as well as participate in financial corruptions and affiliate with any political group. But, in contrary to the special resolution and bylaw, you prepared an illegal decree (regulation) in collaboration with your political groups, which will enable you: (a) to separate the Church from the mother Church's Holy Synod (i.e. to use the Church's funds and assets without 2 accountability); (b) to isolate the Church from the other Ethiopian Orthodox Churches in the UK; and (c) to ban clergymen and regular members of our Church and trying to stop from going to other churches and in parallel, the other churches' clergymen not to come to our Church. This is also entirely divergent and contrary to the Canonical Law of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church, unless you are determined to run the Church as a private business centre only for few individuals, who have already financial vested interest and hatred/divisive political views.

5. Especially, due to our tolerance of not taking a legal action against your past evil and illegal activities in assuming that you will come to your sense, may remorse and become to respect the church's rules as time goes and we may also solve our internal problems by our means. However, you are determined to continue your usual illegal activity/work in more vicious and aggressive way as demonstrated by your actions, to mention some as example:

a) You have illegally banned Deacon Dirshaye Lemma from the Church services and membership of the Clergy Council with a letter called "a legal decision released from the Parish Council" dated on September 19, 2010, with your signature and stamp. You also passed the letter to your groups and unknown governmental bodies. This is the violation of the Church clergymen and members' right stated in the Church's bylaw, Article 48 (1 & 2). In accordance with the Article, you and the Parish Council have no legal authority at all to ban any clergyman or member of the Church.

b) On November 28, 2010, you denounced and persecuted Deacon Dirshaye Lemma who has been serving our Church for over 18 years, standing in the holy place of the Church at the Sunday mass service with false and unfounded allegations. This is not only contrary to our church's Bylaw, Article 48, but to the rule of our Lord Jesus Christ, because, even if, in your opinion, Deacon Dirshaye has made a mistake, his case must be dealt with following the right disciplinary procedures on the basis of our church's bylaw or spiritual rule. In this regard, you have clearly demonstrated that you are in denial of Jesus Christ's teachings (Mat 18:5) in favour of your material interest. Furthermore, you made a false statement in the holy place in front of the congregation stating that the Clergy Council and Joint Council of sub-committees made a decision on D. Dirshaye, while the Clergies Council has never discussed on this matter what so ever so far, and the other sub-committees never exist almost in the last two years. Even those (Building and Development committee members) who claim that they are still working have no mandate to discuss any issue as a member of the Joint Council, as their term of office expired one year a go.

c) As you know, our Church has established rules and regulations to handle and administer any complaints or conflict of interest arise among clergymen and lay members. However due to your failure to deal with complaints of clergymen and members following the rules and regulations, it is known that some members of our Church have taken their complaints and concerns to external legal authorities to seek justice. For example, most recently one regular member (female) of our Church has made a complaint of serious allegation of sexual abuse against one clergyman to the police station that could have been settled according to our Church's rules and regulations through the Clergy Council by imposing spiritual punishment or /repentance on the person who is found guilty. As a consequence of your failure to do that: (a) the case has been taken to the court; (b) the alleged victim member of the Church, whom Christ has died for has fled the Church; (c) this indicates that you seem to have a command-chain or cover-up for any abuse committed by any clergyman or lay member of the Church, as long as they are loyal to you; and (d) our Church may be seen and labelled as a crime seen, instead of a place of forgiveness, peace and reconciliation.

Although you have been repeatedly advised and warned in the past by the Clergy Council, Law and Order Council and other members of the church, you have failed to put those advices and warning notices into practice. We have therefore, been forced to give you this final advice and 3 warning letter to immediately stop your illegal, discriminatory, and divisive/bigotry activities and take the following measures and solutions.

1) As you are well aware, you have no other option left rather than to regret and ask forgiveness as soon as possible in front of the congregation, on the basis of our Christian teaching (Mat 5:23) for all your misconducts and transgressions that harmed /hearted specific clergymen and members in particular and the Church in general before they or we will be forced to take all the cases to the concerning legal authorities seeking justice.

2) The Parish Council members /trustees' election must be held as soon as possible in accordance with the Church's bylaw and trust deeds, since it is long overdue.

3) The alleged corruptions and embezzlement of the Church's funds and assets/properties must be investigated by independent committee elected by the general congregation and the outcome has to be made public straight after.

4) The main reason for the wide spread alleged corruptions, infringement of the rules and regulations/bylaw and other illegal activities is due to the dismantlement or non-existence of the key institutions (the Clergy Council, Law and Order Council and internal Inspection and Control committee). Therefore, fresh election for members of such committees has to be held urgently in accordance with the Church's Bylaw.

5) The case of the member of the Church who was forced to take a legal action in the court because of the failure of the Priest in-charge to deal with the complaint has to be investigated by independent Clergy Council members in accordance with the Church's Bylaw, Article 48, and we have to prove that our Church is a place of love, peace and forgiveness and reconciliation not a place of abuse, corruption, hatred/bigotry.

6) As we all know our Church is under the jurisdiction of the Holy Synod in Ethiopia. This also clearly stated in our Church's Bylaw, Trust Deeds and Special Resolution regarding Patriarch Abba Paulos. But, you have written a new illegal decree that enable you to
7) separate the Church from the mother Church and to isolate it from other Ethiopian Orthodox Churches in the UK. This is entirely contrary to the Canon Law of the Ethiopian Orthodox Tewahido Church. We now strongly believe that your action would be considered as gross misconduct and violation of the Church's Cannon Law that leads you to be banned from serving in any Ethiopian Orthodox Tewahido Churches anywhere under the jurisdiction of the Holy Synod in Ethiopia. We would therefore, strongly advise you to renounce immediately your illegal action and respect the rules and regulations of the Church.

However, if you fail again to respond positively to this warning letter within 14 days by showing your future commitment to implement in full all the suggested solutions (1–6), we will be obliged to take all the cases to the concerning legal authorities and take a legal action against you and other individuals who have been implicated or have involved in these issues.

May Our Lord bless and save our Church!!

Clergies and lay members of the church, Ethiopian Orthodox Tewahido Church, St Mary of Debre,Tsion. (Signatures on Amharic version of this document, from page 3 - 4).

Cc: Lavender Hill, Police Station

ከላይ ከገጽ 1 - 3 ያለውን አንብቤ አምኜበት ፈርሜአለሁ፤
ከርዕሰ/አ/አ/ደ/ጽ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን

| ተ.ቁ (No) | ስም (Name) | ፊርማ (Signature) |
|---|---|---|
| 11 | N. N. Bekele | |
| 12 | A. Kidane | |
| 13 | B. Abebe | |
| 14 | Yohannes Demmelash | |
| 15 | Asnake Tefdanu | |
| 16 | NEGUSU DAWIT | N. Dawit |
| 17 | Tehayou Debebe | |
| 18 | G. Mekonnen | |
| 19 | K. DEMMELASH | |
| 20 | Ms. M. KEBEDE | M.KEBEDE |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

4/4

ከላይ ከገጽ 1 - 3 ያለውን አንብቤ አምኜበት ፈርሜአለሁ፤
ከርዕሰ/አ/ሊ/ደ/ጽ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን

| ተ.ቁ (No) | ስም (Name) | ፊርማ (Signature) |
|---|---|---|
| 21 | Mr G. AMDE | [signature] |
| 22 | Mr P. MICHAEL | [signature] |
| 23 | Ms. A. Assefa | [signature] |
| 24 | Miss. H. Mokes | [signature] |
| 25 | Ms. A. Assefa | [signature] |
| 26 | Mr. F. BEKIR | [signature] |
| 27 | Mr. Y. KUMSA | [signature] |
| 28 | Y. Kumsa | [signature] |
| 29 | F. Yimam | [signature] |
| 30 | N. Eshetu | [signature] |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |
| | | |

ከላይ ከገጽ 1 - 3 ያለውን አንብቤ፣ ለቤ/ክኔ ሰላም ስል አምኜበት ፈርሜአለሁ፤
ከርዕሰ/አ/ሊ/ጳ/ጵ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን

| ተ.ቁ (No) | ስም (Name) | ፊርማ (Signature) |
|---|---|---|
| 31 | M. BarKNHE | |
| 32 | A BerKnh | |
| 33 | M kebede | |
| 34 | M. Getahew | Mesfin Getahun. |
| 35 | S. Limenh | Seife Limenh. |
| 36 | H-BELAY | |
| 37 | Y Adal | |
| 38 | G Adal | |
| 39 | A. Ababe. | |
| 40 | H. MARIAM | |

4/3

ከላይ ከገጽ 1 - 3 ያለውን አንብቤ አምኜበት ፈርሜአለሁ፤
ከርዕሰ/አ/ለ/ደ/ጽ/ቅ/ማርያም የኢ/ኦ/ተ/ቤተክርስቲያን ካህናትና ምእመናን

| ተ.ቁ (No) | ስም (Name) | ፊርማ (Signature) |
|---|---|---|
| 41 | ፑ. Kedede | [signature] |
| 42 | G Zewdie | [signature] |
| 43 | Y. Adenew | [signature] |
| 44 | S. KASSA | Semayew Kassa. |
| 45 | A. Solomon | [signature] |
| 46 | M. Belyneh | MBelyneh. |
| 47 | R. Asfaw | [signature] |
| 48 | B. Bekele | [signature] |
| 49 | T. Kebede | [signature] |
| 50 | S. Atnafu | [signature] |
| 51 | M. Tadesse | [signature] |
| 52 | A. Adane | [signature] |
| 53 | R. Girma | [signature] |
| 54 | M. Worku | [signature] |
| 56 | A. TADESSE | [signature] |
| 57 | H. Admawsu | [signature] |
| 58 | t. tsegaye | [signature] |
| 59 | F. Girma | [signature] |
| 60 | E. Mekonen | [signature] |

4/4